# አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

# የመምህር መምሪያ

# 7ኛ ክፍል


**አዘጋጆች፡-**

ዘላለም መለሰ

ዝናሽ ሰለሞን

እንዬ ጀንበሬ

**አርታኢ፡-**

ዓይን አዲስ አንተነህ

**ጥራት ተቆጣጣሪዎች፡-**

እንግዳ ዘውዴ (ዶ/ር)

አወቀ ጸጋዬ

**የማጣሪያ ንባብ፡-**

ኢሳያስ ይልማ

# ማውጫ


መግቢያ ............ III

ምዕራፍ አንድ ............ 1

የሀገር ፍቅር ............ 1

ምዕራፍ ሁለት ............ 11

ኮቪድ 19 ............ 11

ምዕራፍ ሦስት ............ 22

የአየር ንብረት ............ 22

ምዕራፍ አራት ............ 31

ሥርዓተ ፆታ ............ 31

ምዕራፍ አምስት ............ 41

ኑ ግብር እንክፈል ............ 41

ምዕራፍ ስድስት ............ 51

ሳይንስና ቴክኖሎጂ ............ 51

ምዕራፍ ሰባት ............ 61

ልዩ ፍላጎት ............ 61

ምዕራፍ ስምንት ............ 69

ሱስና መዘዙ ............ 69

ምዕራፍ ዘጠኝ ............ 78

ሀገር በቀል ዕውቀቶች ............ 78

ምዕራፍ አስር ............ 85

አጭር ልቦለድ ............ 85

# መግቢያ

ይህ የመምህር መምሪያ፣ የሰባተኛ ክፍልን መርሃ ትምህርትና የተማሪውን መጽሐፍ መሠረት አድርጎ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚያስተምሩ መምህራን የተዘጋጀ ነው፡፡ ዓላማውም መምህራን የተማሪውን መጽሐፍ ተረድተው በማስተማር ረገድ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል እገዛ ማድረግ ነው፡፡

የመምህር መምሪያው የምዕራፉን ትምህርት ለማቅረብ በተመጠኑ ክፍለ ጊዜያት የተደራጀ ሲሆን ክፍለ ጊዜያቱ ከትምህርቶቹ ጋር እንዲጣጣሙ ተደርገዋል፡፡ ይህ ይባል እንጂ የምዕራፉን ትምህርቶች በዓይነትም ይሁን በመጠን እንደ አመቺነቱ በተሰጡት ክፍለ ጊዜያት ሸንሽኖ ማብቃቃቱ የመምህራን ድርሻ መሆኑ አይካድም፡፡ ይህን ለማድረግ ግን ለመምህሩ መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

በዚህ የመምህር መምሪያ በእያንዳንዱ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች ተዘርዝረዋል፡፡ እነዚህ ውጤቶች በመምህራን እገዛና ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚደረስባቸው ግቦች ናቸው እንጂ ለተማሪው ብቻ የሚተው ግዳጆች አይደሉም፡፡ በሌላ በኩል መምሪያው በእያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ ከክፍለ ጊዜ ትምህርቶች የሚጠበቁ ውጤቶችንና ዝርዝር ይዘቶቻቸውን አቅርቧል፡፡ እነዚህ ሁለት መሰረታዊ ቁምነገሮች በሁለት ረድፍ ተለይተው በሠንጠረዥ የተመለከቱ ሲሆኑ በመጀመሪያው ረድፍ የክፍለ ጊዜው ትምህርት ርዕስ ቀድሞ ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች ተዘርዝረዋል፡፡ በትይዩው ሁለተኛ ረድፍ የክፍለ ጊዜው ትምህርት ዝርዝር ይዘቶች ቀርበዋል፡፡ ከክፍለ ጊዜው የሚጠበቁ ውጤቶችና ዝርዝር ይዘቶች በባለ ሁለት ረድፍ ሠንጠረዥ ጎን ለጎን እንዲታዩ የሆነበት

ምክንያትም ሁለቱንም በአንድ ጊዜ በአንድ ቦታ በማግኘት ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያመች ነው፡፡

እያንዳንዱ ምዕራፍ የራሱ የሆኑ የትምህርት ይዘቶችና የአቀራረብ ስልቶች አሉት፡፡ የትምህርት ይዘቶቹና የአቀራረብ ስልቶቹ ከተማሪው መማሪያ መጽሐፍ አደረጃጀት ጋር በከፍተኛ ጥንቃቄ እየተመሳከሩ የተቀናበሩ ናቸው፡፡ በየምዕራፉ የሚገኙ ትምህርቶች በንዑስ ይዘትነት እራሳቸውን የቻሉ የማስተማሪያ ዘዴዎችና የአቀራረብ ስልቶች አሏቸው፡፡ ለየትምህርቶቹ በየምዕራፉ ይዘት ላይ ተመስርተው በየወገናቸው የተለዩ የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጽሐፍ ክሂሎች እንዲሁም የሰዋስውና የስነ ጽሑፍ ዕውቀትን ለማዳበር የሚያስችሉ ተገቢ ስልቶችና ዘዴዎች ተነድፈውላቸዋል፡፡ ስልቶቹና ዘዴዎቹ የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂሎች የሰዋስውና የስነ ጽሑፍ ዕውቀት ከማዳበር በተጨማሪ አእምሮአቸውን የማሰልጠንና አስተሳሰባቸውን የማበልጸግ ፋይዳም አላቸው፡፡ ከዚህም አልፎ ተማሪዎች ማህበረ ባህላዊ ዐውዶቻቸውን እንዲረዱ እድል የሚሰጡ ናቸው፡፡ እነዚህ የማስተማሪያ ዘዴዎችና የአቀራረብ ስልቶች በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የሚገኙት እንደ አማራጭ ሊያገለግሉ ነው፡፡ የመማር ማስተማር መሳሪያዎች የማይታረሙ፣ የማይለወጡና የማይተኩ አድርጎ ማሰብ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለዚህ መምሪያው የመምህራንን የፈጠራ ጥረትና የክፍል ውስጥ ነጻነት ሊያሰፋና ሊያበለጽግ እንጂ ሊያዳክም አይገባም፡፡ በመሆኑም መምህራን ተማሪዎቻችሁ እንደሚገኙበት ባህላዊና ማህበራዊ ዐውድ ከዘዴዎቹና ከስልቶቹ ጋር እያስማማችሁና እያወደዳችሁ ተጨማሪ ዘዴዎችንና ስልቶች መንደፍ ይኖርባችኋል፡፡

የመምህር መምሪያው በእያንዳንዱ ምዕራፍ እላይ ከጠቀስናቸው ነጥቦች በተጨማሪ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን እንደ አስፈላጊነቱ የመገምገሚያ

ነጥቦችንና ለናሙናነት የቀረቡ የጥያቄ መልሶችን ያካተተ ነው። መርጃ መሳሪያዎቹ የምዕራፉን ትምህርት ቀና ያደርጋሉ ተብለው የታመኑ ስዕሎችን፣ ሰንጠረዦችን እና ቻርቶችን እንደአስፈላጊነቱ የሚጠቁሙ ናቸው። መምህራን ትምህርቱን ከተማሪዎቻችሁ ማህበረ ባህላዊ ዐውድ ጋር እያዛመዳችሁ አዳዲስ መርጃ መሣሪያዎችን ግልጋሎት ላይ እንድታውሉ ይጠበቃል። የመገምገሚያ ነጥቦቹ መምህራን ተማሪዎቻችሁ በየምዕራፉ ማብቂያ ላይ የሚጠበቅባቸውን ውጤቶች ማሳካት አለማሳካታቸውን ለማረጋገጥ ያግዟችኋል። እነዚህ ነጥቦች በየምዕራፉ ያሉትን ይዘቶችና ተግባራት መሠረት በማድረግ የቀረቡ በመሆናቸው ከተግባራቱና ከይዘቶቹ ጋር በማገናዘብ እንድትጠቀሙባቸው ይጠበቃል። ናሙና መልሶቹ ለጥያቄዎቹ በቂና ብቸኛ ምላሾች ላይሆኑ ይችላሉ። አንዳንዶቹ ጥያቄዎች እዚህ ከቀረበው በሰፊው መልኩ ሊመለሱ መቻላቸውን ማጤን ይገባል።

በመጨረሻም የመምህር መምሪያ ማለት በእናንተ በመምህራን እጅ ብቻ የሚገኝና ለተማሪዎች የማይሰጥ መሆኑን እንድትገነዘቡ ያስፈልጋል።

መልካም የሥራ ዘመን እንዲሆንላችሁ እንመኛለን!

# የአንደኛው ወሰነ-ትምህርት

# ምዕራፍ አንድ

# የሀገር ፍቅር

**(6 ክፍለ ጊዜያት)**

## 1.1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች፣ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ፡-

- ስለሀገር ፍቅር ያዳመጡትን ይናገራሉ፤
- ስዕሎችን ተመልክተው የተረዱትን ይናገራሉ፤
- አንብበው የጽሑፉን ይዘት ያስረዳሉ፤
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጣሉ፤
- ጅምር ሀሳቦችን አጠናቀው ይጽፋሉ።

## 1.2. ከክፍለ ጊዜ ትምህርቶች የሚጠበቁ ውጤቶችና ዝርዝር ይዘቶች፡-

| የሚጠበቁ ውጤቶች | ዝርዝር ይዘቶች |
|---|---|
| **ትምህርት አንድ፡-**<br>• ስለሀገር ፍቅር የቀረበውን ምንባብ አዳምጠው ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፤ | • ስለሀገር ፍቅር የቀረበውን ምንባብ አዳምጦ ጥያቄዎችን መመለስ |
| **ትምህርት ሁለት፡-**<br>• ስዕሎችን ተመልክተው የተረዱትን ይናገራሉ፤ | • ስዕሎችን ተመልክተው የተረዱትን መናገር |
| **ትምህርት ሦስት፡-**<br>• የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር ግጥምን እያነበቡ ይዘምራሉ፤ | • የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር ግጥምን እያነበቡ መዘመር |
| **ትምህርት አራት ፡-**<br>• አንብበው የተረዱትን የጽሑፍ ይዘት ያስረዳሉ፤ | • አንብበው የተረዱትን የጽሑፍ ይዘት ማስረዳት |
| **ትምህርት አምስት**<br>• ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጣሉ፤ | • ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት |
| **ትምህርት ስድስት ፡-**<br>• ጅምር ሀሳቦችን አሟልተው ይጽፋሉ፡፡ | • ጅምር ሀሳቦችን አሟልቶ መጻፍ |

## 1.3. የትምህርቱ ይዘትና አቀራረብ

## ሀ ማዳመጥ

### ትምህርት አንድ፡- ስለሀገር ፍቅር የቀረበውን ምንባብ አዳምጦ ጥያቄዎችን መመለስ

ይህ ምዕራፍ የትምህርቱ መጀመሪያ እንደመሆኑ በቅድሚያ የመጽሐፉን መግቢያ ግልጽ ያድርጉላቸው፡፡ በማስከተል ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ከእነርሱ ምን እንደሚጠበቅ አንብበው እንዲረዱ ጊዜ ቢሰጣቸው መልካም ነው፡፡

በመጀመሪያው የትምህርት ክፍል "**ሀገር መውደድ ማለት**" በሚል ርዕስ በመምህሩ መምሪያ የቀረበው ጽሑፍ እርስዎ የሚያነቡት ነው፡፡ ጽሑፉን ከማስደመጥዎ በፊት በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረቡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች በአጭሩ በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ ቀጥሎም በማዳመጥ ሂደት ተማሪዎች እንግዳ ቃላት ሲያጋጥሟቸው በማስታወሻቸው እንዲይዙና ንባቡ ሲጠናቀቅ እርስዎን እንዲጠይቁ ይንገሩዋቸው፡፡ ከንባቡ በኋላ ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዳሉ አሳስበው ድምጽዎን ከፍ አድርገው ንባብዎን ይጀምሩ፡፡ በሚያነቡበት ጊዜ ተማሪዎች በትኩረት እየተከታተሉዎት መሆኑን ያረጋግጡ፡፡

### ከሚደመጠው ምንባብ የወጡ ቁልፍ ቃላትና መልሶቻቸው

እሴት፡- ሊከበሩና ዋጋ ሊሰጣቸው የሚገቡ የማህበረሰብ ሀብቶች

መዘፈቅ፡- ችግር ውስጥ መግባት

አንጥሮ፡- በጥንቃቄ ለይቶ

ጽሑፉን አስደምጠው ከጨረሱ በኋላ በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ በቀረቡት የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች ላይ ተወያይተው ምላሻቸውን በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

## *ሀገር መውደድ ማለት…*

*ሀገር መውደድ ማለት ሁሌም ለሀገር ወይም ለህዝብ ታማኝ ሆኖ መገኘት ነው፡፡ የሚል ትርጉም ሊሰጠው ይችላል፡፡ ለሀገር ታማኝ መሆን በአንድ ሀገር ውስጥ ለታቀፉ ሰዎች ታማኝ በመሆን የሚገለጥ እሴት ነው፡፡*

*የሀገር መውደድ ስሜት የግድ የሰው ልጆችን ከመውደድ መነሳት ይኖርበታል ፡፡ ባንተ እንዲሆን የማትፈልገውን ነገር በሌሎች እንዲሆን ካለመፈለግ እሴት መነሳት አለበት፡፡ የሀገር ፍቅር መገለጫው እንደጊዜው የተለያየ መሆኑ አይቀርም፡፡ ሆኖም ከዚህ ተለዋዋጭ ከሆነ ጉዳይ አንድ ዘላለማዊ ወይም ቋሚ ነገር ማውጣት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የሀገር መውደድ ጉዳይ ማሰብና ማስተዋልን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡ ሀገርን መውደድ በመሰረታዊነት በእሴቶችና በመርሆች ዙሪያ የሚመሰረት አመለካከት ነው፡፡ ይህ የማይለዋወጥ የሀገር ፍቅር ስሜት ባህሪ ነው፡፡ ሀገርን የመውደድ ስሜት በየዋህነትና ባለማወቅ ከተመራ አደገኛ ውጤት ይኖረዋል፡፡*

በቀጣዩ የንባብ ክፍል ምን አይነት ሀሳብ የሚቀርብ ይመስላችኋል?

*ሀገር መውደድ ማለት ሰውን መውደድ ማለት ነው፡፡ ለሀገር የሚኖር ታማኝነት ለተራራውና ለወንዙ አይደለም፡፡ ተራራውና ወንዙ ትርጉም የሚኖራቸው ለሰዎች ሲያገለግሉ ነው፡፡ ስለዚህ ሀገርን መውደድ ሰውን ወይም ህዝብን መውደድ ነው፡፡*

ሰው የሚወዳቸውን ነገሮች እያጠፉ ሀገሬን እወዳለሁ ማለት አይቻልም፡፡ ለህዝብ ጥቅም እያሉ ህዝብን የሚጎዳ ተግባር ውስጥ መዘፈቅ ሀገርን የሚያሳንስ ተግባር ነው፡፡ ሀገርን መውደድ ትውልዱ ባለበት ዘመን ሀገር ምን እንደምትፈልግ ማወቅን ይጠይቃል፡፡ ሀገርን የመውደድ ስሜት መነሻ ሊደረግ የሚገባው በዘመኑ ሀገር በምን ችግር ውስጥ እንደሆነች በመረዳት የተደቀነባትን ችግር አፍኖ እንዳያስቀራት አስተውሎ ለመራመድ የሚያስችላትን እሴት አንጥሮ በማውጣት አደጋዎችን እያስተዋሉ ለመንዝ መጣጣር ነው፡፡ ስለዚህ እሴቶቻችንን በመጠበቅ ለሰው ልጅ ክብርና ፍቅር መስጠት ከእያንዳንዱ ሰው የሚጠበቅ የዜግነት ኃፊነት ነው፡፡

(ምንጭ፡- ከድረ ገጽ የተወሰደና ለማስተማር እንዲስማማ ተደርጎ የተቀናበረ)

# ለ መናገር

## ትምህርት ሁለት፡- ስዕሎችን ተመልክቶ መናገር

መምህር/ት፣

በዚህ ክፍል ተማሪዎች የሚያከናውኑት ተግባር ስዕሎችን ተመልክቶ መናገር ሲሆን በተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ስዕሎች እንዲመለከቱ ያድርጉ፡፡ ቀጥሎም ከስዕሉ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በእርስዎ መሪነት ይመልሱ፡፡ ሌሎች የሀገር ፍቅር ስሜት ሊገለጽ የሚችልበትን ተግባር የሚያሳዩ ስዕሎችን ያሳዩዋቸውና ስለምንነታቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

# ሐ ማንበብ

## ትምህርት ሦስት፡- የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር ግጥምን እያነበቡ መዘመር

መምህር/ት፡-

ከዚህ በታች የቀረበውን የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር በጥቁር ሰሌዳ ላይ ለተማሪዎች ይጻፉላቸው፡፡ ከዚያም የመዝሙሩን ግጥም እያነበቡ መዝሙሩን በጋራ እንዲዘምሩ ያድርጉና ስለ ግጥሙ መልዕክት ከጓደኞቻቸው ጋር ተወያይተው እንዲነግሩዎት ያድርጉ፡፡

### የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር

የዜግነት ክብር በኢትዮጵያችን ፀንቶ
ታየ ህዝባዊነት ዳር እስከዳር በርቶ
ለሰላም ለፍትህ ለህዝቦች ነፃነት
በእኩልነት በፍቅር ቆመናል ባንድነት
መሰረተ ፅኑ ሰብዕናን ያልሻርን
ህዝቦች ነን ለስራ በስራ የኖርን
ድንቅ የባህል መድረክ ያኩሪ ቅርስ ባለቤት
የተፈጥሮ ፀጋ የጀግና ህዝብ እናት
እንጠብቅሻለን አለብን አደራ
ኢትዮጵያችን ኑሪ እኛም ባንቺ እንኩራ፡፡

## ትምህርት አራት፡- አንብበው የተረዱትን የጽሑፍ ይዘት ማስረዳት

መምህር/ት፣

በዚህ ክፍል "የሀገር ፍቅር በምን ይገለጻል?" በሚል ርዕስ የቀረበው ጽሑፍ ተማሪዎች ድምፅ ሳያሰሙ በየግል የሚያነቡት ነው። ንባቡን ከመጀመራቸው በፊት በቅድመ ንባብ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ይምሯቸው። ጥያቄዎቹ ተማሪዎች ስለሚያነቡት ምንባብ ግምት እንዲኖራቸው የሚያደርጉና በምንባቡ የሚነሳውን ጉዳይ የሕይወት ገጠመኛቸው አካል ሆኖ እንዲሰማቸው የሚያደርጉ ናቸው። በንባባቸው ሂደትም ንባባቸውን ገታ አድርገው የንባብ ሂደት ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያሳስቧቸው።

ከድህረ ንባብ ጥያቄዎች የመጀመሪያው ቀደም ብሎ በነበረው የትምህርት ክፍል ስለሀገር ፍቅር መገለጫዎች የተገለጸውን ሀሳብ በማጠናከር ደጋግመው እንዲያስቡበት የቀረበ ነው። የመጀመሪያው ጥያቄ በሌሎች የትምህርት አይነቶች ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ከሚማሩት ትምህርት ጋር የሚገናኝና ስለሀገራቸው የጀግንነት ታሪኮች በንባብ ካገኙት መረጃ በመነሳት አስፍተው እንዲያስቡበት የሚጋብዝ ነው። ቀሪዎቹ ጥያቄዎችም ከንባብ ያገኙትን መረጃ ከሕይወታቸው ጋር አገናኝተው ችግር ፈቺ ሀሳቦችን እንዲያመነጩ የሚጋብዙ መሆናቸውን ልብ ይበሉ። በመሆኑም ሰፋ ያለ ጊዜ በመያዝ ጥያቄዎቹን እንዲመልሱ ያድርጉ።

መምህር/ት፡-

ከድህረ ንባብ ጥያቄዎች ተከትሎ በቀረበው ተግባር ተማሪዎች ግጥሙን አንብበው ከግጥሙ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ያድርጉ።

# መ ቃላት

## ትምህርት አምስት፡- ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት

መምህር/ት፣

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺን እንዲሰጡ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም በተግባር አንድ ቃላትን በዐውድ ለማስተማር "ሰላም ዋጋው ስንት ነው?" በሚል ርዕስ በሀገራችን ወቅታዊ የሆነውን ሰላም በተመለከተ የቀረበ ምንባብ ነው፡፡ ተማሪዎች ምንባብ አንብበው ለተሰመረባቸው ቃላት እንደ አገባባቸው ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡ እግረ መንገዳቸውንም ስለቀረበው ርዕሰ ጉዳይ ሀሳብ እንዲያንሸራሽሩ ይምሯቸው፡፡ በተግባር ሁለት ደግሞ ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡባቸው የቀረቡትን ቃላት በምሳሌው መሰረት ያሰሯቸው፡፡

እዚህ ላይ ልብ ሊሉት የሚገባው ነገር በማስታወሻ ክፍል እንደተገለጸው የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ማለት በቃላት መካከል ፍፁም የሆነ የትርጉም አንድነት ማለት እንዳልሆነ ነው፡፡ በመሆኑም የቃላት ፍቺ አንጻራዊ በመሆኑ በተለያየ ዐውድ ለቃሉ የሚሰጡ ፍቺዎች የተለያዩ ሊሆኑ እንደሚችሉ ያስገንዝቧቸው፡፡ ከዚያም በተግባር አንድ ለተሰጡት ቃላት ይቀርባል የሚሉትን ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

# ሠ መጻፍ

## ትምህርት አምስት፡- ጅምር ሀሳቦችን አሟልቶ መጻፍ

በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ከሀገር ፍቅር ዐውድ ሳይወጡ እንዲያሟሏቸው የቀረቡ በጅምር የቀሩ ሀሳቦች አሉ፡፡ የተጓደሉትን ዐረፍተ ነገሮች ከራሳቸው አሳብ

አፍልቀው አሟልተው እንዲጽፏቸው ያድርጉ። በማስከተልም ስራቸውን ተመልክተው የጽሑፍ ግብረ መልስ ይስጧቸው።

## 1.4. መርጃ መሳሪያዎች

- የሀገር ፍቅር መገለጫ ተግባራትን የሚያሳዩ ልዩ ልዩ ስዕሎች (ለምሳሌ የአባይ ግድብን የሚያሳይ ስዕል፣ በተለያዩ ተግባራት የተሰማሩ ታታሪ ሰራተኞችን የሚያሳይ ስዕል፣ ወዘተ.)
- ተመሳሳይ ፍቺን የሚያሳይ ቻርት

## 1.5. ግምገማ

- ስለሀገር ፍቅር ባዳመጡት መሠረት ጥያቄዎችን በትክክል መመለሳቸውን ማረጋገጥ፤
- በቡድን ውይይት ተግባር በአግባቡ መሳተፋቸውን መከታተል፤
- ስለሀገር ፍቅር መገለጫዎች አንብበው የተረዱትን የጽሑፍ ይዘት በንግግር ማስረዳት መቻላቸውን ማረጋገጥ፤
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን መገምገም፤
- ጅምር ሀሳቦችን ከራሳቸው አፍልቀው ማሟላታቸውን መከታተል።

## 1.6. ናሙና የጥያቄ መልሶች

**መ ቃላት**

ትምህርት አራት

**ተግባር 1**

የቃላት ፍቺ

| ቃላት | የቃላቱ ፍቺ |
|---|---|

| | |
|---|---|
| 1.አርበኝነት | ጀግንነት፣ሀገር ወዳድነት |
| 2.መከባበር | አንዱ ለሌላው ዋጋ መስጠት |
| 3.መስዋዕትነት | ለሌሎች የሚከፈል ዋጋ |
| 4.በጎነት | መልካምነት |
| 5.መለገስ | መስጠት |
| 6.ሉአላዊነት | እራሱን ማስተዳደርና መምራት የሚችል |
| 7.ብልጽግና | እድገት፣ ከፍ ማለት |

**ሠ መጻፍ**

ትምህርት አምስት

ተግባር

ጅምር ሀሳቦችን አሟልቶ መጻፍ

1. ሰንደቅ አላማ **የአንድ ሀገር ክብር መገለጫ ነው**፡፡
2. የመንግስትና የህዝብ ሀብትን መንከባከብ **ከሁሉም ዜጋ የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው**፡፡
3. ጠንክሮ በመስራት ድህነትንና ኋላቀርነትን **መዋጋት ይቻላል**፡፡
4. የተራቆቱ አካባቢዎችን በደን መሸፈን **አፈር ተሸርሽሮ እንዳይሄድ ይከላከላል**፡፡
5. የኢትዮጵያ አርበኞች ሀገራቸውን ከወራሪ ለመከላከል **ብዙ መስዋዕትነትን ከፍለዋል**፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ኮቪድ 19
## (7 ክፍለ ጊዜያት)

## 2.1. የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

ተማሪዎች፣ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ፡-

- ባዳመጡት መሠረት ክፍት ቦታዎችን ያሟላሉ፤
- ስለወቅታዊ ጉዳይ አዳምጠው ክርክርና ምልልስ ያደርጋሉ ፤
- ስለ ኮቪድ-19 አንብበው የተረዱትን ይናገራሉ፤
- ኮቪድ-19 ንን በተመለከተ የግል ተሞክሮዎቻቸውን ይናገራሉ፡፡
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ይሰጣሉ፤
- ምዕላዶችን ያጣምራሉ፤ይነጥላሉ፤
- ነጠላና ድርብ ዐረፍተ ነገሮችን ይመሠርታሉ፡፡

## 2.2. ከክፍለ ጊዜ ትምህርቶች የሚጠበቁ ውጤቶችና ዝርዝር ይዘቶች፡-

| የሚጠበቁ ውጤቶች | ዝርዝር ይዘቶች |
|---|---|
| ትምህርት አንድ፡-<br>• በንባብ የቀረበ ጽሑፍን አዳምጠው የተጓደሉ ቦታዎችን ያሟላሉ፤ | • በንባብ የቀረበ ጽሑፍን አዳምጦ የተጓደሉ ቦታዎችን ማሟላት |
| ትምህርት ሁለት፡-<br>• በንባብ የቀረበ ጽሑፍን አዳምጦ ምልልስና ክርክር ማቅረብ | • በንባብ የቀረበ ጽሁፍን አዳምጦ ምልልስና ክርክር ማቅረብ |
| ትምህርት ሦስት፡-<br>• ስለ ኮቪድ 19 አንብበው የተረዱትን ይናገራሉ፤ | • ስለ ኮቪድ 19 አንብበው የተረዱትን መናገር |
| ትምህርት አራት፡-<br>• ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ትሰጣላችሁ፤ | • ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት |
| ትምህርት አምስት፡-<br>• ምዕላዶችን ያጣምራሉ፤ ይነጥላሉ፤ | • ምዕላዶችን ማጣመርና መነጠል |
| ትምህርት ስድስት፡-<br>• ነጠላና ድርብ ዐረፍተ ነገሮችን ትመሰርታላችሁ፡፡ | • ነጠላና ድርብ ዐረፍተነገሮችን መመስረት |

## 2.3. የትምህርቱ ይዘትና አቀራረብ

### ሀ ማዳመጥ

### ትምህርት አንድ፡- በንባብ የቀረበ ጽሑፍን አዳምጦ የተጓደሉ ቦታዎችን ማሟላት

መምህር/ት፣

በዚህ የትምህርት ክፍል በቀረበው ተግባር ተማሪዎች በንባብ የቀረበ ጽሑፍን አዳምጠው የተጓደሉ ቦታዎችን እንዲያሟሉ ይጠበቃል። በዚህም መሰረት በቅድሚያ የሚጠበቁባቸውን ውጤቶች አንብበው ጥያቄዎች ካሉዋቸው እንዲጠይቁ ያድርጉ። በመቀጠል በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ተማሪዎችን ለማዳመጥ ተግባር ለማነቃቃት ይረዳ ዘንድ የኮቪድ 19 የ "መ" ህጎችን የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ ቀርቧል። ተማሪዎች ስዕሉን በመመልከት የተረዱትን እንዲናገሩ ያድርጓቸው። በስዕሉ የተገለጹት የ "መ" ህጎች **መራራቅ፣ መታጠብ፣ መቆየትና መሸፈን** ናቸው።

በማስከተል **"የዳንቾ ስጋት"** በሚል ርዕስ የቀረበውን ጽሑፍ ድምፅዎን ከፍ አድርገው ከማስደመጥዎ በፊት ከምንባቡ የወጡ ቁልፍ ቃላትን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉና ከተማሪዎች ጋር በመወያየት ለቃላቱ ፍቺ ይስጡ። ለውይይቱ ይረዳዎት ዘንድ የቃላቱ ፍቺ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ለተማሪዎች የሚያስደምጡት ጸሑፍ በተማሪ መጽሐፍ ላይ በየመሀሉ የተጓደሉ ሀሳቦች ያሉበት ሆኖ የቀረበ ነው። እርስዎ ጽሑፉን ሲያነቡላቸው ተማሪዎች በጥሞና እያዳመጡ የተጓደለውን ሀሳብ በተገቢዎቹ ቃላትና ሀረጋት በጽሑፍ እንዲያሟሉ ያድርጉ። በመጨረሻም መልሳችውን እጅ በማውጣት እንዲነግሩዎት ያድርጉ። እንዲሟሉ የተመረጡት ቃላትና ሀረጋት እርሶ እንዲያነቡት በቀረበው ጽሁፍ ጎላ ብለው ከስራቸው ተሰምሮባቸዋል።

# የዳንቾ ስጋት

ወይዘሮ ዳንቾ በጌዴኦ ዞን ቡሌ በምትባል የገጠር ከተማ በቤቷ ውስጥ ምግብ እያዘጋጀች በመሸጥ **አራት ልጆቿን** የምታስተዳድር ታታሪና ንቁ እናት ናት፡፡ በሰሞኑ ግን አንድ አእምሮዋን እያስጨነቀ ሰላም የነሳት ጉዳይ **በየመገናኛ ብዙሀኑ** ሲነገር በተደጋጋሚ እየሰማች ነው - የኮሮና በሽታ፡፡ የስራዋ ጸባይ የበለጠ ለበሽታው ተጋላጭ እንደሚያደርጋት ተረድታለች፡፡ ግን **እራሷንና ቤተሰቧን** ከሚባለው በሽታ ለመጠበቅ በትክክል ምን ማድረግ እንዳለባት አላወቀችም፡፡ ድንገት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ዱሪቲ ትዝ አለቻት፡፡ ጊዜ ሳታባክን ዱሪቲን ለማናገር ከቤቷ ስትወጣ ዱሪቲ **መደበኛ ስራዋን** ለመስራት ስትጓዝ አገኘቻትና ደስ አላት፡፡ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ዳንቾ ለምን እንደፈለገቻት በመግለጽ ጥያቄዋን ጀመረች፡፡

ዳንቾ፡- ለመሆኑ ይህ ኮሮና በሽታ ምንድን ነው?

ዱሪቲ፡- የኮሮናቫይረስ በሽታ ከቀላል እስከ ከባድ **የመተንፈሻ አካል** ሕመም የሚያስከትል በሽታ ነው፡፡ ይህ በሽታ የሚመጣው **በቫይረስ** ነው፡፡ በሽታው እንደ ጉንፋን ዓይነት ቀላል ምልክቶችን አሳይቶ በራሱ ሊድን ወይም ሊባባስ እና እንደሳንባ ምች፣ከባድ የመተንፈሻ አካላት ሕመም ብሎም የኩላሊት ስራን **በማስተጓጎል** ሞትን ሊያስከትል የሚችል እና በዓለም ላይ በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፋ የሚገኝ በሽታ ነው፡፡

ዳንቾ፡- ወይ ጉድ ይገርማል፡፡ ለመሆኑ በምንድን ነው ሚተላለፈው?

ዱሪቲ፡- መተላለፊያ መንገዶቹ የተለያዩ ናቸው፡፡ በበሽታው የታመሙ ሰዎች በሚያስነጥሱበትና በሚያስሉበት ጊዜ ከታማሚው ሰው ከትንፋሽ ጋር የሚወጡ

እርጥበት አዘል **ብናኞች** ወደ ጤነኛው ሰው አፍናና አፍንጫ ሲገቡ፣ ከታማሚው ሰው ጋር ንክኪ ሲደረግ ለምሳሌ እጅ በመጨባበጥ፣ ንጽህናው ባልተጠበቀ እጅ ዓይን፣ አፍንጫና አፍን መነካካት፣ ያልበሰሉ የእንስሳት እና የዓሳ ምግቦችን መመገብ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ዳንኞ፡- ገባኝ፣ ግን በበሽታው የተያዘውን ሰው እንዴት እናውቃለን?

ዱሪቲ፡- የበሽታው ምልክቶች ትኩሳት፣ማሳ፣የትንፋሽ ማጠር፣የጉሮሮ መከርከር፣ ለመተንፈስ መቸገር ናቸው፡፡

ዳንኞ፡- በጣም ከበድ ነው ባክሽ ! እሺ እንዴት መከላከል ይቻላል?

ዱሪቲ፡- መከላከያዎቹ በቀላሉ ሊደረጉ የሚችሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ እጅ አለመጨባበጥ፣ አለመሳሳምና አለመተቃቀፍ፣ እጅን በሳሙናና በውሃ ቶሎ ቶሎ በደንብ መታጠብ፤ እጅን በአግባቡ በሳሙናና በውሃ ሳይታጠቡ **ዓይንን፣ አፍንጫንና አፍን** አለመነካካት፣ በበሽታው የታመመ ሰው ካለ አለመጨባበጥ ወይም የቅርብ ንክኪ አለማድረግ እና ቢያንስ ሁለት የአዋቂ እርምጃ ያህል መራቅ፤ ህዝብ በተሰበሰበበት አካባቢ አለመገኘት፣ በሚያስነጥሱበትና በሚያስሉበት ጊዜ አፍና አፍንጫን በታጠፈ ክንድ መሸፈን፣ የተጠቀሙበትን ሶፍት ክዳን ባለው ዕቃ በአግባቡ አስቀምጦ ማስወገድ ናቸው፡፡

ዳንኞ፡- ግን ድንገት በበሽታው የተያዘ ሰው ቢኖር ምንድን ነው መደረግ ያለበት?

ዱሪቲ፡- ጥሩ ጥያቄ ነው፡፡ በበሽታው የተያዘ ሰው ቢያጋጥም ቶሎ ወደ ህክምና ጣቢያ መሄድ እና ለሌሎች ሰዎች በሽታውን እንዳያስተላልፍ ደግሞ እራሱን **አግልሎ** ከ10 እስከ 15 ቀን አንድ ክፍል ውስጥ ለብቻው መቆየት አለበት፡፡

**ዳንኞ፡- አመሰግናለሁ ዱሪቲ፣ በጣም ጥሩ ትምህርት ነው የሰጠሽኝ፡፡ የነገርሽኝን ሁሉ በማድረግ <u>እራሴንና ቤተሰቤን</u> ከዚህ አስከፊ በሽታ እጠብቃለሁ፡፡ ደህና ዋይ ዱሪቲ፡፡**

**ዱሪቲ፡- ደህና ዋይ ዳንኞ፤ስለጠየቅሽኝ ደስ ብሎኛል፡፡ ለቤተሰቦችሽና ለጎረቤቶችሽም ይህንኑ ንገሪያቸው፡፡**

(በኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና አገልግሎት በድረ ገጽ ከቀረበ መረጃ ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የቀረበ)

# ለ መናገር

## ትምህርት ሁለት፡- በንባብ የቀረበ ጽሑፍን አዳምጦ ምልልስና ክርክር ማቅረብ

**መምህር/ት፣**

**በመምሪያ መጽሐፍ ላይ ለድህረ ማዳመጥ ተግባር በተሰጠው መመሪያ መሰረት ተማሪዎች በውይይትና በክርክር ሂደቱ በንቃት እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፡፡**

# ሐ ማንበብ

## ትምህርት ሦስት፡- ስለ ኮቪድ 19 አንብበው የተረዱትን መናገር

**መምህር/ት "ድንገተኛው አለም አቀፍ ወረርሽኝ "በሚል ርዕስ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች በየግላቸው በእርጋታ ድምጽ ሳያሰሙ የሚያነቡት ነው፡፡ በቅድሚያ የተማሪዎችን የማንበብ፣ የመማርና የማወቅ ፍላጎት ለመቀስቀስ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በእርስዎ መሪነት ይመልሱ፡፡ በንባቡ ሂደት**

ለሚገጥሟቸው የንባብ ላይ ጥያቄዎች መልስ ነው የሚሉትን በደብተራቸው ላይ በጽሑፍ እያሰፈሩ ማለፍ እንደሚገባቸው ያሳስቧቸው፡፡ ሁሉም አንብበው መጨረሳቸውን እንዳረጋገጡ በንባብ መሀል ጥያቄዎች ላይ በቃል እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡

በድህረ ንባብ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ተማሪዎች አንብበው የተረዱትን እንዲገልጹ የሚረዱ የእውነት ሀሰት፣ የምርጫ ጥያቄዎች እና ተማሪዎች ከምንባቡ ያገኙትን መረጃ ከገጠመኞቻቸው ጋር በማያያዝ የሚመልሷቸው ጥያቄዎች ተሰጥተዋል፡፡ እነዚህን ጥያቄዎች እንዳጠያየቃቸው እንዲመልሱ ይርዷቸው፡፡

## መ ቃላት

## ትምህርት አራት፡- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት

መምህር/ት፣

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡባቸው የቀረቡ ቃላት አሉ፡፡ በእነዚህ ቃላት ፍቺ ላይ ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩና መልሳቸውን እንዲነግሩዎት ያድርጉ፡፡ ቀደም ሲል በምዕራፍ አንድ ስለ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ በቀረበው ትምህርት የቃላት ፍቺ አንጻራዊ መሆኑን በተመለከተ የተነሳውን ሀሳብ ያስታውሱ፡፡ ለቃላት ተመሳሳይም ብቻ ሳይሆን ተቃራኒ ፍቺም ሲሰጥ አንጻራዊ እንጂ ፍፁም የሆነ ተቃርኖ አለመኖሩን ልብ ይበሉ፡፡

# ሠ ሰዋስው

## ትምህርት አምስት፡- ምዕላዶችን ማጣመርና መነጠል

በዚህ ክፍል እንደ መነሻ የቀረቡት ቃላት ተማሪዎች ቃላትን በምዕላዶች ነጥለው እንዲያስቀምጧቸው የተሰጡ ናቸው፡፡ ተማሪዎች ከቀደመ ዕውቀታቸው በመነሳት ቃላቱን በምዕላድ ነጥለው እንዲያስቀምጡ ይርዱዋቸው፡፡ ቀጥሎ በመማሪያ መጽሐፉ ለማጠናከሪያ ይረዳቸው ዘንድ ስለምዕላድ የቀረበውን ማስታወሻ በምሳሌ አስደግፈው ያስረዱዋቸው፡፡ ከዚያም በተግባር አንድ የቀረቡትን የመልመጃ ጥያቄዎች ያሰሩዋቸው፡፡

## ትምህርት ስድስት፡- ነጠላና ድርብ ዐረፍተ ነገሮችን መመስረት

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ነጠላና ድርብ ዐረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ይጠበቃል፡፡ በቅድሚያ ማስታወሻውን በግል እንዲያነቡ ዕድል ይስጧቸው፡፡ ከንባቡ በኋላ ማስታወሻውን ምን ያህል እንደተረዱ ለመመዘን ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸው፡፡ ምላሻቸውን መሠረት በማድረግ ማስታወሻውን ግልጽ ያድርጉላቸው፡፡ በመቀጠል ማስታወሻውን ተከትለው የቀረቡትን ጥያቄዎች ያሰሯቸውና ስራቸውን ተመልክተው ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## 2.4. መርጃ መሳሪያዎች

- የኮቪድ 19 ቫይረስ በቤተሙከራ ሲታይ ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ምስል
- ተነጣጥለው እና ተነጥለው የቀረቡ ቃላትን የሚያሳይ ቻርት
- ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ የሚያሳይ ቻርት
- የተጣመሩ እና የተነጣጠሉ ምዕላዶችን የሚያሳይ ቻርት

## 2.5. ግምገማ

- በንባብ የቀረበ ጽሑፍን አዳምጠው የተጓደሉ ሀሳቦችን በአግባቡ ማሟላታቸውን መከታተል፤
- በንባብ የቀረበ ጽሑፍን አዳምጠው በምልልስና መክርክር በንቃት መሳተፋቸውን መከታተል፤
- ስለ ኮቪድ 19 የቀረበውን ጽሑፍ በግል አንባበው ስለተረዱት ሀሳብ መግለጽ መቻላቸውን መገምገም፤
- ለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን መገምገም፤
- በቃል ውስጥ ነጻና ጥገኛ ምዕላዶችን ለይተው ማስቀመጣቸውን ማረጋገጥ፤
- ነጠላና ድርብ ዐረፍተ ነገሮችን መመስረታቸውን ማረጋገጥ።

## 2.6. ናሙና የጥያቄ መልሶች

### ሐ ማንበብ

ትምህርት ሦስት፡-

ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

1. እውነት/ሀሰት

   ሀ. እውነት

   ለ. እውነት

   ሐ. እውነት

   መ. እውነት

   ሠ. ሀሰት

2. የምርጫ ጥያቄዎች

   1. መ

   2. ሐ

   3. መ

## መ ቃላት

ትምህርት አምስት፡-

ተግባር

የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ

| ቃል | ተመሳሳይ ፍቺ | ተቃራኒ ፍቺ |
|---|---|---|
| ሀ. ትኩሳት | የሰውነት ሙቀት መጨመር | የሰውነት መቀዝቀዝ |
| ለ. መከሰት | መፈጠር | አለመፈጠር |
| ሐ. ተባባሰ | ጨመረ | ጠፋ |
| መ. ማስተዋል | በጥልቀት ማሰብ | አለማገናዘብ |
| ሠ. ተጋላጭ | ችግሩ የሚያገኘው፣ተጠቂ የሆነ | ችግሩ የማያገኘው፣ ከችግሩ የተጠበቀ |
| ረ. መዘናጋት | ችላ ማለት | ትኩረት መስጠት |
| ሰ. ህመም | በበሽታ ምክንያት የሚፈጠር ስሜት | ጤንነት |
| ሸ. ሰለባ | ተጎጂ | ጉዳት ያልነካው |

## ሠ. ሰዋስው

ትምህርት ስድስት፡-

ተግባር

ምዕላዶችን ማጣመርና መነጠል

1.

| ቃል | ነጻ ምዕላድ | ጥገኛ ምዕላድ |
|---|---|---|
| ሀ. ቫይረሶች | ቫይረስ | -ኦች |
| ለ. ምልክቶች | ምልክት | -ኦች |
| ሐ. ሴቶች | ሴት | -ኦች |
| መ. ስሜቶች | ስሜት | -ኦች |
| ሠ. በሬዎች | በሬ | -ዎች |

2.

| ምዕላዶች | | |
|---|---|---|
| ነጻ ምዕላድ | ቅጥያዎች | ቃል |
| ልብስ | -ኤ | ልብሴ |
| ተጋላጭ | -ኦች | ተጋላጮች |
| ፈተና | -ህ | ፈተናህ |
| ምግብ | -ኣችን | ምግባችን |
| ደረቅ | -ኦች | ደረቆች |

# ምዕራፍ ሦስት

# የአየር ንብረት

**(12 ክፍለ ጊዜያት)**

## 3.1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች፣ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- አዳምጠው የተረዱትን ይናገራሉ፤
- የድምፅ ጥብቀትን አዳምጠው ይለያሉ፤
- በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ንግግር ያደርጋሉ፤
- በዐረፍተ ነገር ውስጥ ሥርዓተ ነጥቦችን ይጠቀማሉ፤
- የተለያዩ የንባብ ስልቶችን ይለያሉ፤
- ግጥም አንብበው ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ይሰጣሉ፤
- የቃል ክፍሎችን ይለያሉ፡፡

## 3.2. ከክፍለ ጊዜ ትምህርቶች የሚጠበቁ ውጤቶችና ዝርዝር ይዘቶች፡-

| የሚጠበቁ ውጤቶች | ዝርዝር ይዘቶች |
|---|---|
| **ትምህርት አንድ፡-**<br>• አዳምጠው የተረዱትን ይናገራሉ፤ | • አዳምጠው የተረዱትን መናገር |
| **ትምህርት ሁለት፡-**<br>• የድምጽ ጥብቀትን አዳምጠው ይለያሉ፤ | • የድምጽ ጥብቀትን አዳምጦ መለየት |
| **ትምህርት ሦስት፡-**<br>• በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ንግግር ያቀርባሉ፤ | • በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ንግግር ማቅረብ |
| **ትምህርት አራት፡-**<br>• የንባብ ስልቶች ይለያሉ፤ | • የንባብ ስልቶችን መለየት |
| **ትምህርት አምስት ፡-**<br>• ግጥምን አንብባችሁ ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ትሰጣላችሁ፤ | • ግጥምን አንብቦ ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት |
| **ትምህርት ስድስት**<br>• ሥርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ ይገለገላሉ፤ | • ሥርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ መገልገል |
| **ትምህርት ሰባት ፡-**<br>• የቃል ክፍሎችን ትለያላችሁ፤ | • የቃል ክፍሎች መለየት |

# ሀ ማዳመጥ

## ትምህርት አንድ፡- አዳምጠው የተረዱትን መናገር

መምህር/ት፣

እንደተለመደው በቅድሚያ ተማሪዎች የሚጠበቁባቸውን ውጤቶች አንብበው ጥያቄዎች ካሏቸው እንዲጠይቁ ዕድል ይስጧቸው፡፡ ለጥያቄዎቹ ምላሽ ከሰጡ በኋላ ወደምዕራፉ ቀዳሚ ተግባር ይሸጋገሩ፡፡ ተማሪዎች ምንባቡን ከማዳመጣቸው በፊት በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የቀረቡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች በቃል ይመልሱ፡፡ በማስከተልም "**ምድር በአስፈሪ ሁኔታ እየሞቀች ነው**!" በሚል ርዕስ የቀረበውን ጽሑፍ ለተማሪዎች ድምጽዎን ከፍ አድርገው ያንብቡላቸው፡፡

በንባብ ሂደት ተግባር ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ በመያዝ በንቃት እንዲያዳምጡና በእርስዎ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ አዳምጠው ሲጨርሱም የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያድርጓቸውና ለምላሾቻቸው ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎቹ የማዳመጥ ክሂል ከንግግር ክሂል ጋር ተጣምሮ የሚቀርብበትና በተጠየቃዊ አስተሳሰብ ችግር ፈቺ ሀሳቦችን እንዲያፈልቁ የሚጋብዝ በመሆኑ በቂ ጊዜ ይስጧቸው፡፡

### ምድር በአስፈሪ ሁኔታ እየሞቀች ነው!

ተመራማሪዎች እንደሚሉት በቅርቡ መቋቋም የማንችለውን ሙቀት ምድራችን ታስተናግዳለች፤ የምድር የውሃ አካላትም ከፍታቸው ይጨምራል፡፡ ምንም እንኳን የካርቦን ዳይ ኦክሳይድ መጨመርን ለመቆጣጠር የአለም ሃገራት ስምምነት ላይ ቢደርሱም፣ የምድር ሙቀት ከእለት ወደ እለት እየጨመረ መጥቷል፡፡ በዚህ መስክ ምርምር ያደረጉ ባለሙያዎች የሰሩት ጥናት እንደሚያመላክተው የምድር

ሙቀት በየአመቱ 2 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ የሚጨምር ከሆነ፤ የሁላችንም ስጋት የሆነው ከፍተኛ ሙቀትና ተያያዥ ችግር አይቀሬ ይመስላል።

የምድር ሙቀት 2 ዲግሪ ሴልሺየስና ከዚያ በላይ ከሆነ ምድር ከምቹ መኖሪያነት ወደ ጠላትነት ትቀየራለች። በአሁኑ ጊዜ የምድር ሙቀት በሚያስፈራ ሁኔታ በየአመቱ እየጨመረ ነው። የከፋ ከሚባል አይነት አደጋ ሰዎችን እየጠበቁ ያሉት ደግሞ ትላልቅ ጫካዎች፤ እየቀለጠ የሚገኘው የአርክቲክ ባህር የበረዶ ግግር እና የውቅያኖሶች ቅዝቃዜ ናቸው።

በጥናቱ መሰረት የከፋ ጉዳት ከመድረሱ በፊት መከላከል ይቻላል። ነገር ግን ከእራሷ ከምድር ጋር ከፍተኛ የሆነ እርቅ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ይጠቁማል። የሰውን ልጅ በከፍተኛ ሁኔታ እያሳሰቡ ያሉት የአየር ንብረት ለውጥና ሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች አጠቃላይ የምድርን ተፈጥሯዊ ሂደት እየጎዱት እንደሆነ ማስተዋል ይቻላል። ይህ ማለት ደግሞ ከምድራችን ጋር ያለንን ግንኙነት ካስተካከልን የወደፊቱን እጣ ፈንታ ማስተካከል እንችላለን ማለት ነው።

እንደ መፍትሔ ተብለው የተቀመጡት ደግሞ ለተለያዩ ግልጋሎቶች ብለን የምናቃጥላቸውን ነገሮች መቀነስ፣ ብዙ ዛፎችን መትከል፣ ጥቅጥቅ ደኖቻችንን መንከባበከብና ካርቦንዳይኦክሳይድን አካባቢ አየር መምጠጥ የሚችሉ የፈጠራ ውጤቶችን ማበረታታት ተጠቃሾች ናቸው።

(ምንጭ፡-ቢቢሲ አማርኛ መስከረም 25 2017)

## ትምህርት ሁለት፡- የድምጽ ጥብቀትን አዳምጦ መለየት

መምህር/ት፣

በዚህ ክፍል ተማሪዎች በቃላት ውስጥ ጠብቀውና ላልተው የሚጠሩ ድምጾችን አዳምጠው እንዲለዩና ትርጉማቸውን እንዲናገሩ የቀረበውን አንቀጽ እርስዎ ያነብቡላቸው፡፡ ጠብቀውና ላልተው ስለሚነገሩ ቃላት ግንዛቤ ይፈጥርላቸው ዘንድ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ መቋጫ በማድረግም ትምህርቱን ያጠቃሉ፡፡

# ለ መናገር

## ትምህርት ሦስት፡- በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ንግግር ማቅረብ

መምህር/ት፣

በዚህ የትምህርት ክፍል ተማሪዎች የንግግር አቀራረብ መመሪያን ተከትለው ንግግር ማድረግ እንዲለማመዱ ይጠበቃል፡፡ ስለንግግር አቀራረብ መከተል የሚገባቸውን መመሪያ በመማሪያ መጽሐፍ የቀረበውን አጭር ማስታወሻ መነሻ በማድረግ ያስረዱዋቸው፡፡ ቀጥሎ የአየር ንብረት ለውጥን በሚመለከት አንድ ርዕስ እንዲመርጡ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያም በመረጡት ርዕስ ላይ በቡድን ተወያይተው የተስማሙበትን ሀሳብ አደራጅተው ከቡድናቸው አንድ ሰው በመወከል በተማሩት የንግግር አቀራረብ መመሪያ መሰረት ለክፍል ተማሪዎች ንግግር እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ለሰሩት ሥራም ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

# ሐ ማንበብ

## ትምህርት አራት፡- የንባብ ስልቶችን መለየት

*መምህር/ት፡-*

በዚህ ክፍል ተማሪዎች የተለያዩ የንባብ ስልቶችን እንዲለዩና የተወሰኑትን ደግሞ በክፍል ውስጥ እንዲለማመዷቸው ይጠበቃል፡፡ የንባብ ስልቶችን ምንነትና ዓላማ በተመለከተ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረበውን አጭር ማስታወሻ መነሻ በማድረግ በጥያቄና መልስ ተማሪዎችን ያሳተፈ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ በመቀጠል **"የአየር ንብረት"** በሚል ርዕስ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረበውን ምንባብ በመጠቀም የአሰሳ ንባብንና ጥልቅ ንባብን ለመለማመድ የሚረዱትን መልመጃዎች በክፍል ውስጥ እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ ስራቸውንም በመከታተል ገምግመው ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## ትምህርት አምስት፡- ግጥምን አንብቦ ለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት

*መምህር/ት፣*

በዚህ ክፍል የቀረበው ግጥም ተማሪዎች በግላቸው አንብበው በግጥሙ ውስጥ ለሚገኙ ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ የሚሰጡበት ነው፡፡ እርስዎም ይህንኑ በመረዳት በመልመጃ አንድና በመልመጃ ሁለት የቀረቡትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

# መ መጻፍ

## ትምህርት ስድስት፡- ሥርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ መገልገል

መምህር/ት፣

በዚህ ክፍል በአማርኛ ጽሑፍ ውስጥ በስፋት ከምንገለገልባቸው ሥርዓተ ነጥቦች አራቱን በማቅረብ በጽሑፍ ውስጥ እንዴት እንደምንገለገልባቸው ተማሪዎች እንዲለዩ ቀርቦላቸዋል፡፡ ስለትምህርቱ ግንዛቤ ይፈጥርላቸው ዘንድም በመጽሐፋቸው ላይ አጭር ማስታወሻ ቀርቧል፡፡ ተማሪዎችን በጥያቄና መልስ በደንብ በማሳተፍ ስለ ሥርዓተ ነጥቦቹ ዓይነትና አጠቃቀም በርከት ያሉ ምሳሌዎችን በመጠቀም ያስረዷቸው፡፡ በማስከተል በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረቡትን የመልመጃ ጥቄዎች ያሰሯቸው፡፡

# ሠ ሰዋስው

## ትምህርት ሰባት፡- የቃል ክፍሎችን መለየት

መምህር/ት፣

ይህ የትምህርት ክፍል ከአምስቱ የአማርኛ የቃል ክፍሎች በሦስቱ ላይ ትኩረት በማድረግ የቀረበ ነው፡፡ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ስለ እነዚህ የቃል ክፍሎች የቀረበውን በምሳሌዎች የተደገፈ ማስታወሻ መነሻ በማድረግ ትምህርቱን ተማሪዎችን በሚያሳትፍ ሁኔታ ያቅርቡላቸው፡፡ በማስከተል በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረቡትን የመለማመጃ ተግባራት በክፍል ስራና በቤት ስራ መልክ ያሰሯቸውና ለስራቸው ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## 3.3. መርጃ መሳሪያዎች

- በሙቀት መጨመር የተጎዱ ቦታዎችን የሚያሳይ ምስል
- የሚጠብቁ ድምፆች ያሉባቸውን ቃላት የሚያሳይ ቻርት

- በተለያዩ የንባብ አይነቶች ሊነበቡ የሚችሉ ጽሑፎች (ለምሳሌ ለአሰሳ ንባብ የስልክ ቁጥር ማውጫ፣ዓ/ምና የቦታ ስሞች ያሉበት ጽሑፍ)፣ለገረፍታ ንባብ ጋዜጣ ወይም መጽሔት፣ ለሰፊ ንባብ የተለያዩ ልቦለዶች
- በትምህርትነት ለቀረቡት ሥርዓተ ነጥቦች ማሳያ የሚሆኑ ልዩ ልዩ ጽሑፎች
- የቃል ክፍሎችን ማሳያ ቻርት

## 3.4. ግምገማ

- የድምጽ ጥብቀትን አዳምጠው መለየታቸውን ማረጋገጥ
- በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የንግግር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ንግግር ማቅረባቸውን ማረጋገጥ
- የንባብ ስልቶችን መለየታቸውን መከታተል
- ግጥምን አንብበው ለቃላት ተመሳሳና ተቀራኒ ፍቺ መስጠታቸውን መከታተል
- ሥርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ መጠቀማቸውን ማረጋገጥ
- የቃል ክፍሎችን መለየታቸውን መገምገም

## 3.5. ናሙና የጥያቄ መልሶች

### መ መጻፍ

ትምህርት ስድስት፡-

ተግባር

1. የሀገር ውስጥ ፍጆታ ማለትም ሳሙና፣ ዘይት፣ ሸቀጣሸቀጦች፣ ጥራጥሬዎች ዋጋቸው በእጥፍ ጨምሯል፡፡

2. አካባቢው በአበቦች አጊጧል፤ የሳሩ ልምላሜ ቀልብን ይሰውራል፤ የህጻናቱ ቡረቃ ሀሴትን ይፈጥራል፤ የክረምቱ ወራት መጠናቀቁ ሳይሆን አይቀርም።
3. ጀግና ነው! ያንን ሁሉ ፈተና አልፎ ተሸላሚ ሆነ!

## ሠ. ሰዋስው

### ትምህርት ስድስት

ተግባር

| | ስም | ቅጽል | ግስ |
|---|---|---|---|
| ሀ. አደገኛው ወንጀለኛ ተፈረደበት። | ወንጀለኛ | አደገኛው | ተፈረደበት |
| ለ. ጠይሟን ልጅ እወዳታለሁ። | ልጅ | ጠይሟን | እወዳታለሁ |
| ሐ. ፈጣን መኪና ያስፈልገኛል። | መኪና | ፈጣን | ያስፈልገኛል |
| መ. አጭበርባሪው ነጋዴ ከሰረ። | ነጋዴ | አጭበርባሪው | ከሰረ |
| ሠ. ሰፊው ጫካ ተመነጠረ። | ጫካ | ሰፊው | ተመነጠረ |
| ረ. ሀይለኛ ጉንፋን ይዞኛል። | ጉንፋን | ሀይለኛ | ይዞኛል |

# ምዕራፍ አራት

# ሥርዓተ ፆታ

(9 ክፍለ ጊዜያት)

## 4.1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች፣ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ሥርዓተ ፆታን የተመለከተ ምንባብን አዳምጠው የተረዱትን ይገልጻሉ፡፡
- በታቀደ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተቀናጀ ንግግር ያደርጋሉ፡፡
- ቃላትን ለመረዳት ጽሑፍን ያነባሉ፡፡
- አጣማሪዎችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ ይጠቀማሉ፡፡
- የዐረፍተ ነገር ክፍሎችን ይለያሉ፤
- በዐረፍተ ነገር ደረጃ ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በትክክል ይጠቀማሉ፡፡

## 4.2. ከክፍለ ጊዜ ትምህርቶች የሚጠበቁ ውጤቶችና ዝርዝር ይዘቶች፡-

| የሚጠበቁ ውጤቶች | ዝርዝር ይዘቶች |
|---|---|
| **ትምህርት አንድ፡-**<br>• ስለ ሥርዓተ ፆታ አዳምጠው የተረዱትን ይናገራሉ፤ | • ስለ ሥርዓተ ፆታ አዳምጠው የተረዱትን መናገር |
| **ትምህርት ሁለት፡-**<br>• በታቀደ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተቀናጀ ንግግር ያቀርባሉ፤ | • በታቀደ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተቀናጀ ንግግር ማቅረብ |
| **ትምህርት ሦስት፡-**<br>• ቃላትን ለመረዳት ያነባሉ፤ | • ቃላትን ለመረዳት ማንበብ |
| **ትምህርት አራት፡-**<br>• አጣማሪዎችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ ይጠቀማሉ፤ | • አጣማሪዎችን በአረፍተ ነገር ውስጥ መጠቀም |
| **ትምህርት አምስት ፡-**<br>• የዐረፍተ ነገር ክፍሎችን ይለያሉ፤ | • የዐረፍተ ነገር ክፍሎችን መለየት |
| **ትምህርት ስድስት ፡-**<br>• ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል ይጠቀማሉ፡፡ | • ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል ይጠቀማሉ፡፡ |

## 4.3. የትምህርቱ ይዘትና አቀራረብ

## ሀ ማዳመጥ

### ትምህርት አንድ፡- ስለ ሥርዓተ ፆታ አዳምጠው የተረዱትን መናገር

መምህር/ት፣

ተማሪዎችዎ በቅድሚያ የሚጠበቁባቸውን ውጤቶች ያንብቡ። ጥያቄም ካላቸው እንዲጠይቁ ይጋብዟቸውና ለጥያቄዎቹ ምላሽ ይስጡባቸው። **"መንፈሰ ጠንካራዋ አሚና"** የሚለው ምንባብ የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ለማሳደግና ለመመዘን ታስቦ የቀረበ በመሆኑ እርስዎ ድምጽዎን ከፍ አድርገው ያንብቡላቸው። በመጀመሪያ ግን ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የቀረበውን ስዕል በትኩረት ተመልክተው የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያድርጉ። ከዚያም በማዳመጥ ሂደት እርስዎ ሲያነቡላቸው ዋና ዋና ነጥቦችን በመጻፍ በንቃት እንዲያዳምጡ ያድርጉ። ሲጨርሱም የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ።

**መንፈሰ ጠንካራዋ አሚና**

እንደምንናችሁ ውድ ተማሪዎች? እ…አሚና እባላለሁ። ከወረዳችን የሴቶች ጉዳይ ቢሮ ጋር በመተባበር በማህበረሰባችን ውስጥ ከሴቶች ጋር በተያያዘ በልማድ የሚደረጉ ጎጂ ድርጊቶችን በትምህርት ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት ውስጥ በበጎ ፍቃድ አገለግላለሁ። እ… ለዚህ ተግባር ምን አነሳሳሽ ብትሉኝ፣ መልሴ እኔም በአንድ ወቅት የጥቃት ሰለባ መሆኔ ነው።

ከኔ ጋር ናችሁ አይደል? አ…ዎ ይኸውላችሁ ተማሪዎች፣ የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩ፣ ጥቃቱ ሲደርስብኝ። የምማርበት ትምህርት ቤት ከቤታችን ትንሽ

ርቀት ነበረው፡፡ አሁንም እዚህ መሀል ከሩቅ አካባቢ መጥታችሁ የምትማሩ ሴት ተማሪዎች እናዳላችሁ አውቃለሁ፡፡ እውነት ነው አይደል? አ… ዎ እና እንደሁልጊዜው ትምህርት ቤት ውዬ ስመለስ ባልጠበኩት አጋጣሚ በማላውቃቸው ሰዎች በጉልበት ተወስጄ የመደፈር ጥቃት ደረሰብኝ፡፡ ይህንን የምነግራችሁ ከኔ ህይወት እንድትማሩ ነው፡፡ ሁኔታው በጣም ከባድ ነበር፡፡ ጥቃቱ ያልተፈለገ እርግዝና ይዞብኝ መጣ፡፡ እ… ፈታኝ ጊዜ ነበር፡፡ ትምህርቴን ለማቋረጥ ተገደድኩ፤ ባላሰብኩት ሁኔታ የልጅ እናት ሆንኩ፡፡ በሁኔታው ከፍተኛ የስነልቦና ቀውስ ውስጥ በመግባቴ ለረጅም ጊዜ ከቤት አልወጣሁም ነበር፡፡

ቤተሰቦቼም ሁኔታዬ በጣም ስላሳሰባቸው የባለሙያ ምክር እንዳገኝ ወደ ህክምና ወሰዱኝ፡፡ ከባለሙያ በማገኘው ምክርና ክትትል ቀስ በቀስ ጤንነቴ እየተመለሰ ቤተሰቦቼም ስነልቦናዬን በመገንባት እያበረታቱኝ ያቋረጥኩትን ትምህርቴን እንደአዲስ ቀጠልኩ፡፡ ጥቃቱን ያደረሱብኝ ሰዎችም በህግ ተጠያቂ ሆነው ረጅም ጊዜ ስለተፈረደባቸው እስካሁን በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡ እኔም በትምህትርቴ በመግፋት ዩኒቨርሲቲ ገብቼ፣ በህግ ትምህርት ተመርቄ በአሁኑ ሰአት በአቃቤ ህግ ሙያ ማህበረሰቤን በማገልገል ላይ እገኛለሁ፡፡ በዚህ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የተሰማራሁበት ምክንያትም እንደናንተ ያሉ ሴት ልጆች ለዚህ አይነት ችግር እንዳይዳረጉ ለመከላለልና ጉዳቱ የደረሰባችውም ተስፋ ቆርጠው እቤታቸው እንዳይቀመጡ የራሴን የህይወት ታሪክ በማጋራት ለማበረታታት ነው፡፡ ተረድታችሁኛል አይደል? አ…ዎ ልጆች እርስ በርሳችን መደጋገፍና መማማር አለብን፡፡ እናንተ የነገ ሀገር ተረካቢ የሀገር ተስፋዎች ናችሁ፡፡ ህብረተሰባችንን በተሻለ መንገድ ወደ ፊት ለማራመድ በትምህርት ውስጥ ካለን ሰዎች ብዙ ይጠበቃል፡፡ አይደለም እንዴ? በጣም ጥሩ!

ሴቶችን ከጥቃት መጠበቅና በተለያዩ ተግባራት ማሳተፍ አስፈላጊ የሚሆነው ለምን ይመስላችኋል? አያችሁ ተማሪዎች፣ በገጠርም ሆነ በከተማ ካለው የህዝብ ብዛት ሴቶች ግማሹን ቁጥር ይይዛሉ፡፡ ሴቶችንና ወንዶችን እኩል የማያሳትፍ እና ተጠቃሚ የማያደርግ ማንኛውም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ለውጤት አያበቃም፡፡ ከታሪካችን እንደምንረዳው ሴቶች በተለያዩ ሁኔታዎች በሚደርስባቸው አድሎ ወይም ልክ በኔ እንደደረሰው አይነት ጠባሳም እንዲካካስ ልዩ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ ለዚህ ደግሞ ወንዶችም ሴቶችም እኩል ትኩረት ልንሰጠው ይገባል፡፡ ልክ ነኝ ወንዶች? በጣም ጥሩ!

የፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥና ሴቶችን ከኢኮኖሚ ጥገኝነት ለማላቀቅ በዙሪያችን ባሉ ዘርፎች በትምህርት፣ በጤና፣ የስራ እድልን በመፍጠር ሴቶችን ማገዝ ተገቢ ነው፡፡ ኧ... እንደማህበረሰብ በጋራ ለመለወጥ ሴቶችን በገቢ ማስገኛ ስራዎች ማሳተፍ፣ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ እና ሀብት የማፍራት እና የመጠቀም፣ በኛ ሀገር ብዙም የተለመደ ባይሆንም በቤተሰብ ውስጥ እኩል የስራ ድርሻ መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም በማንኛውም ረገድ ሴቶች የሚደርስባቸው ጥቃት የሚወገድበትን ስልት መቀየስ ያስፈልጋል፡፡ ኧ... ይህንን የምነግራችሁ ከራሳችሁ አልፋችሁ ቤተሰቦቻችሁን በማስተማር የኖርንበትን ጎጂ ልማድ እንድትዋጉት ነው፡፡ ስህተታችንን በማረም እኛ የዛሬ ትውልዶች ነገን ለሴቶችም ለወንዶችም የተሻለ ማድረግ እንችላለን፡፡ አንችልም? እንችላለን! ታዲያ እነዚህን ጎጂ ልማዶች ለመለወጥ በቁርጠኝነት መታገል ይኖርብናል፡፡ ዛሬ ያለነው እኛ ነን፡፡ እኛ ለለውጥ መሰረት መጣል ከቻልን የነገው ትውልድ ደግሞ በተሻለ ሁኔታ ይጨርሰዋል፡፡ አይደለም እንዴ ልጆች? ለዛሬ እዚህ ላይ ይበቃናል፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ በድጋሚ እንገናኛለን፡፡ ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

(ምንጭ፡- ከአዘጋጆቹ)

# ለ መናገር

## ትምህርት ሁለት፡- በታቀደ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተቀናጀ ንግግር ማቅረብ

መምህር/ት፣

በዚህ ክፍል ሁለት የንግግር ተግባራት ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያው ቀደም ብሎ በማዳመጥ ትምህርት ክፍል ስለ ሥርዓተ ፆታ ከተማሩት በመነሳት ችግር ፈቺ ሀሳብ የሚያመነጩበት ነው፡፡ ስለዚህ በእርስዎ መሪነት ቡድን መስርተው እንዲወያዩና የተስማሙበትን ሀሳብ ከየቡድኑ ሁለት ተማሪዎችን በመወከል ሀሳባቸውን ለክፍል ተማሪዎች የንግግር ሥርዓትን በመከተል እንዲያቀርቡ ያግዟቸው፡፡

ሁለተኛው ተግባር ተማሪዎች በቡድናቸው ቤታቸው ወስደው የሚሰሩት ሲሆን በሚኖሩበት አካባቢ ቀደም ሲል በማዳመጥ ክፍል ካዳመጡት የአሚና ዓይነት ችግር የገጠመው ሰው ታሪክ አጠያይቀው ጽፈው እንዲለማመዱና ከቡድናቸው አንድ ተማሪ ወክለው ለክፍል ጓደኞቻቸው ንግግር እንዲያቀርቡ ይንገሯቸው፡፡

# ሐ ማንበብ

## ትምህርት ሦስት፡- ቃላትን ለመረዳት ማንበብ

መምህር/ት፣

በዚህ ክፍል “**ሥርዓተ ፆታ**” በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ተማሪዎች በግላቸው እንዲያነቡትና በኋላም በቡድን እንዲወያዩበት የቀረበ ነው፡፡ ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረቡትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በእርስዎ መሪነት እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ ቀጥሎም በማዳመጥ ሂደት ተማሪዎች ምንባቡን እያነበቡ በየመሀሉ የተሰመረባቸውን ቃላትና ሀረጋት በአገባባቸው መሰረት ፍቻቸውን ለመረዳት እንዲሞክሩ ያድርጓቸው፡፡

በማስከተልም የድህረ ንባብ ተግባሩን ለመስራት እንዲችሉ የክፍሉን ተማሪዎች በስድስት ቡድን ያስቀምጧቸው፡፡ በመቀጠል የምንባቡን ስድስት አንቀጾች ከፋፍለው ይስጧቸውና በየአንቀጾቹ የተሰመረባቸውን ቃላትና ሀረጋት በአገባባቸው መሰረት የያዙትን ፍቺ መሰረት በማድረግ የአንቀጾቹን መልዕክት እንዲወያዩበት ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም የተረዱትን ሀሳብ ለሌሎች ቡድኖች በእርስዎ መሪነት ያስረዱ፡፡ እርስዎም አዳምጠው ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## መ መጻፍ

### ትምህርት አራት፡- አጣማሪዎችን/አያያዦችን/ በዐረፍተ ነገር ውስጥ መጠቀም

መምህር/ት፣

በዚህ ክፍል አጣማሪዎችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ ስለመጠቀም የሚያስገነዝብ ትምህርት ቀርቧል፡፡ ተማሪዎች ስለርዕሰ ጉዳዩ መጠነኛ ግንዛቤ እንዲይዙ ይረዳቸው ዘንድ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ በማድረግ በምሳሌዎች የተደገፈ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ በመቀጠል ተከትለው የተሰጡ ተግባራትን በመስራት ልምምድ እንዲያደርጉ ይርዷቸው፡፡ ስራዎቻቸውንም በየተራ ይመልከቱላቸው፡፡

## ሠ ሰዋስው

### ትምህርት አምስት፡- የዐረፍተ ነገር ክፍሎችን መለየት

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ሁለቱን መሰረታዊ የዐረፍተ ነገር ክፍሎች እንዲለዩ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ከዚህ በፊት በነበረው የክፍል ደረጃ የተማሩትን በማስታወስ ስማዊ ሀረግንና ግሳዊ ሀረግን እንዲለዩ በሚያደርገው ተግባር ያስጀምሯቸው፡፡ በማስከተልም ትምህርቱን በተመለከተ ለግንዛቤ ይረዳቸው ዘንድ

በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ተማሪዎችን በጥያቄና መልስ በንቃት በማሳተፍ ትምህርቱን ያጠቃልላቸው፡፡

## ትምህርት ስድስት፡- ስዋስዋዊ መዋቅሮችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል መጠቀም

መምህር/ት፣

የዚህ ክፍለ ትምህርት አላማ ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል መጠቀም ማስቻል ነው፡፡ ስለዚህ የመዋቅር ስህተቶችን አስተካክለው እንዲጽፉ የተሰጠውን ተግባር ከቀደመ ዕውቀታቸው በመነሳት እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ ቀጥሎም የጥያቄዎቹን ምላሾች እጅ እያወጡ እንዲመልሱ ይምሯቸውና ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጧቸውና ማስታወሻውን ከነምሳሌው እንዲያነቡ ይምሯቸው፡፡ አንብበው ሲጨርሱ ከተሰጠው ምሳሌ አስረጂ እየወሰዱ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡ ተጨማሪ ምሳሌዎችንም ከራስዎ ይጨምሩላቸው፡፡

## 4.4.መርጃ መሳሪያ

- አጣማሪዎችን ማሳያ የሚሆን ጽሑፍ
- የዐረፍተ ነገር ክፍሎችን ማሳያ ሰንጠረዥ

## 4.5. ግምገማ

- ስለ ሥርዓተ ፆታ አዳምጠው መረዳታቸውን በጥያቄዎች መገምገም፣
- በታቀደ ርዕሰ ጉዳይ የተቀናጀ ንግግር ማቅረባቸውን መከታተል፣
- ካነበቡት ጽሑፍ ውስጥ ለቀረቡ ቃላት ትክክለኛውን ፍቺ መስጠታቸውን ማረጋገጥ፣
- አጣማሪዎችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ መጠቀማቸውን ማረጋገጥ፣

- የዐረፍተ ነገር ክፍሎችን በአግባቡ መለየታቸውን መገምገም፣
- ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል መጠቀማቸውን መከታተል።

## 4.6. ናሙና የጥያቄ መልሶች

### ሀ ማዳመጥ

ትምህርት ሁለት

ተግባር

1. አጣማሪዎችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ መጠቀም

1.1. ይልቁንም

1.2. ስለዚህ

1.3. ይሁን እንጂ

1.4. በመሆኑም

1.5. ነገር ግን

### ሠ. ሰዋስው

ትምህርት አምስት

ተግባር

የዐረፍተ ነገር ክፍሎች

1ሀ. ጥቁሩ ጃኬት / ገመዱ ላይ ተሰቅሏል።
ስማዊ ሀረግ ግሳዊ ሀረግ

ለ. እርጥብ እንጨት / ትላንት ወደከተማ ተጫነ።
ስማዊ ሀረግ ግሳዊ ሀረግ

ሐ. ወጣገባ መንገድ / ለመራመድ አይመችም።
ስማዊ ሀረግ ግሳዊ ሀረግ

መ. <u>ኋላቀር አስተሳሰብ</u> / <u>በትምህርት ይለወጣል፡፡</u>

ስማዊ ሀረግ ግሳዊ ሀረግ

ሠ. <u>አስተዋይ ሰው</u> / <u>ለነገ ያስባል፡፡</u>

ስማዊ ሀረግ ግሳዊ ሀረግ

ሰ. <u>ጨቅጫቃው ወንድሜ</u> / <u>በቅርቡ ይመጣል፡፡</u>

ስማዊ ሀረግ ግሳዊ ሀረግ

ትምህርት ስድስት፡

ተግባር

ስዋስዋዊ መዋቅሮችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል መጠቀም

| | | |
|---|---|---|
| | ምሳሌ፤- ላሚቷ ሳር በላ፡፡ | የፆታ አለመስማማት |
| ሀ. | መሰረት የሌለው ቤት ቶሎ ትፈርሳለች፡፡ | የፆታ አለመስማማት |
| ለ. | በርካታ ነጋዴዎች ትርፋቸው እንደቀነሰ ገለጻችሁ፡፡ | የመደብ |
| ሐ. | የመንደራችን ሽማግሌዎች የተጣሉ ሰዎችን አስታረቀ፡፡ | የቁጥር |
| መ. | ሚልኪ ባሌቤቱን በጣም ያከብሯታል፡፡ | የቁጥር |
| ሠ. | አጎቴ ሰኞ ትመጣለች፡፡ | የፆታ |
| ረ. | የከድር ቤተሰቦች በቅርቡ ሰርግ ለመደገስ ተዘጋጅቷል፡፡ | የቁጥር |
| ሰ. | እናንተ ነገ ለስራ ይፈለጋሉ፡፡ | የመደብ |
| ሸ. | ሙሽራው በጣም አምሮባታል፡፡ | የፆታ |

# ምዕራፍ አምስት

# ኑ ግብር እንክፈል

(10 ክፍለ ጊዜያት)

## 5.1. ሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች፣ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- የተለያየ ድምጸት ያላቸውን ዐረፍተ ነገሮች አዳምጠው ይለያሉ፤
- በድምጽ የተቀረጹ የግብር ማስታወቂያዎችን አዳምጠው ምላሽ ይሰጣሉ፤
- በምልልሶች በንቃት ይሳተፋሉ፤
- የምባቡን ይዘት ይተነትናሉ፤
- አንቀጽ ይጽፋሉ፤
- ጥሩ ተናጋሪዎች ቃላትን እንዴት በትክክል እንደሚጠሩ ይገመግማሉ።

## 5.2. ከክፍለ ጊዜ ትምህርቶች የሚጠበቁ ውጤቶችና ዝርዝር ይዘቶች፡-

| የሚጠበቁ ውጤቶች | ዝርዝር ይዘቶች |
|---|---|
| ትምህርት አንድ፡-<br>• የተለያየ ድምጸት ያላቸውን ዐረፍተ ነገሮች አዳምጦ ይለያሉ፤ | • የተለያየ ድምጸት ያላቸውን ዐረፍተ ነገሮች አዳምጦ መለየት |
| ትምህርት ሁለት፡-<br>• በድምጽ የተቀረጹ የግብር ማስታወቂያዎችን አዳምጠው ምላሽ ይሰጣሉ፤ | • በድምጽ የተቀረጹ የግብር ማስታወቂያዎችን አዳምጦ ምላሽ መስጠት |
| ትምህርት ሦስት፡-<br>• በምልልሶች በንቃት ይሳተፋሉ፤ | • በምልልሶች በንቃት መሳተፍ |
| ትምህርት አራት፡-<br>• የምንባብን ይዘት ይተነትናሉ፤ | • የምንባብን ይዘት መተንተን |
| ትምህርት አምስት ፡-<br>• አንቀጽ ይጽፋሉ | • አንቀጽ መጻፍ |
| ትምህርት ስድስት ፡-<br>• ቃላትን በትክክል ይጠራሉ። | • ቃላትን በትክክል መጥራት |

## 5.3. የትምህርቱ ይዘትና አቀራረብ

## ሀ ማዳመጥ

### ትምህርት አንድ፡- የተለያየ ድምጸት ያላቸውን ዐረፍተ ነገሮች አዳምጦ መለየት

መምህር/ት፣

ቀጥሎ "ታማኙ ምንዳ" በሚል ርዕስ የቀረበው ጽሑፍ እርስዎ ለተማሪዎች በንባብ የሚያስደምጧቸው ነው፡፡ ተማሪዎች ከማዳመጣቸው በፊት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ ቀጥሎም ድምፅዎን ከፍ አድርገው ጽሑፉን በንባብ ያስደምጧቸው፡፡ ተማሪዎች በማዳመጥ ሂደት የጥያቄ ድምጸት ያላቸውን ዐረፍተ ነገሮች ለይተው እንዲናገሩ በየመሀሉ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ ጥያቄው ግልጽ ይሆንላቸው ዘንድ አንድ ሁለት ጥያቄያዊ ዐረፍተ ነገሮችን ከሚያነቡት ጽሑፍ በምሳሌነት በማሳየት የአነባብ ድምጸታቸውን ያስረዷቸው፡፡ ጽሑፉን የማስደመጥ ተግባር ከተጠናቀቀ በኋላ የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

### ታማኙ ምንዳ

ምንዳ አማሮ ከተማ የሚኖር እሳት የላሰ ነጋዴ ነው፡፡ እድሜው በሰላሳዎቹ መጀመሪያ ነው፡፡ ወላጅ አባቱን በልጅነቱ በሞት ስላጣ እናቱ ብቻዋን ነው ያሳደገችው፡፡ በትምህርቱ በደንብ ወደፊት የመግፋት ፍላጎት ቢኖረውም የሚደግፈው ቤተሰብ ስላልነበረ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ አነስተኛ ሱቅ ከፍቶ በሸቀጣሸቀጥ ንግድ ስራ ላይ ተሰማራ፡፡ ምንዳ በጣም ቀልጣፋና ታታሪ ነው፡፡ ስራውን በጀመረ በጥቂት አመታት ውስጥ ከፍተኛ

መሻሻል አሳይቶ የሚሰራበትን ሱቅ ወደ ትልቅ መደብርነት ቀይሮታል። ምንዳ ሱቅ ተፈልጎ የሚጠፋ እቃ የለም።

ምንዳ ጎበዝ ነጋዴ ብቻ ሳይሆን ጎበዝ ግብር ከፋይም ነው። ግብር ተቀባዮችም በታማኝ ግብር ከፋይነቱ በተከታታይ የእውቅና ሰርተፍኬት አበርክተውለታል። በዛሬው እለትም ምንዳ እንደተለመደው ግብር ከፍሎ እየተመለሰ ነው። የመደብሩ በር ላይ ሲደርስ በአቅራቢያው መካከለኛ የሸቀጣሸቀጥ ሱቅ ባለቤት የሆነውን ታደለን አገኘው። ታደለ የምንዳን መምጣት ሲጠባበቅ ነበር። ታደለ በፈገግታ ተሞልቶ ለሰላምታ እጁን እየዘረጋ ‹‹እንዴት ነህ ምንዳ የት ጠፍተህ ነው?›› አለው።

“ሰላምነው ታዴ? ግብር ልክፈል ብዬ ወደ ገቢዎች ወጣ ብዬ መመለሴ ነው።” አለው።

"መቼም ግብር በመክፈል አትታማም። ለመሆኑ የዚህ ትጋት ሚስጥሩ ምንድን ነው?"

"ግብር መክፈልማ ጥቅሙ ብዙ ነው። ምን ይጠየቃል ብለህ ነው።"

"እኛም ያንተን መንገድ ብንከተል ጥሩ ነበር። ያው እንደምታውቀው ንግዳችን ብዙም የሰፋ ስላልሆነ ወደ ግብሩ ብዙም አንጋፈጥም። ከዚች ትንሽ ንግድ ግብር ብንከፍል ምን ይተርፈናል ብለህ ነው።"

“ሀይ ታዴ ንግድህ ትንሽም ሆነ ትልቅ ከምታገኘው ገቢ ላይ እንዳቅምህ ግብር መክፈል አለብህ። እኔን ተመልከተኝ ሱቄ ትንሽ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ግብሬን

በትክክል እከፍላለሁ፡፡ ነገር ግን ከስሬ ሱቁን አልዘጋሁም፡፡ እንዲያውም ንግዴ በጥሩ ሁኔታ አድጎ የትልቅ መደብር ባለቤት ሆኛለሁ፡፡”

“ለመሆኑ ላንተ የገባህ እኛን ያልገባን ነገር ምንድን ነው? እውነቱን ልንገርህ አይደል እኔ አሁን ለግብር የምከፍለው ገንዘብ ያሳዝነኛል፡፡” አለው ታደለ ፈገግ ብሎ፡፡

“ንገረኛ እኔም ልወቀው” አለው ታደለ ፈገግታው ከፊቱ ላይ ሳይጠፋ፡፡

“ሊያሳዝንህ አይገባም ታዴ፣ መቼም በሬዲዮኑም በቴሌቪዢኑም በየጊዜው የምሰማው ነገር ስለግብር ያለኝን አመለካከት እንዳስተካክል ረድቶኛል፡፡” ና ግባ አረፍ ብለን እንጫወታለን አለው ምንዳ በእጁ ወደ ሱቁ ውስጥ እያመለከተው፡፡

“አየህ ታዴ እኛ ያልተረዳነው ነገር የከፈልነው ግብር በተዘዋዋሪ ተመልሶ ለኛው እንደሚመጣ ነው፡፡ ግብር በፈቃደኝነት እና በፍላጎት መከፈል ያለበት የዜግነት ግዴታ ነው፡፡ ግብር ለጋራ ልማት የሚውል ከህዝብ የሚሰበሰብ ገቢ ነው፡፡ መንግስት የምንኖርበትን ሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ አድገትን ለማፋጠን ክፍተኛ ሀላፊነት አለበት፡፡ ይህን ታምናለህ?”

“በሚገባ” አለ ታደለ እራሱን ወደላይና ወደታች እየነቀነቀ፡፡

“ይሄን ሃላፊነት ለመወጣት መንግስት የራሱን ገቢ ከየት ያመጣል፡፡ ግብር ይሄን ስራ የሚያከናውንበት አንዱና ዋነኛው የገቢ ምንጭ ነው፡፡ የተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትንና መንገድ ለመገንባትና ለብሄራዊ ደህንነት የሚውል ገንዘብ ለማግኘት የሚያስችል እንደሆነ ልንገነዘብ ይገባል፡፡ ለዚህም ነው ግብር የአንድ አገር ኢኮኖሚ ልማትና እድገት የጀርባ አጥንት ነው የሚባለው፡፡ በዚህም መሰረት ግብር መክፈል የዜግነት ግዴታ መሆኑን በመረዳት ሁላችንም የሚጠበቅብንን ግብር በወቅቱ መክፈል አለብን፡፡ ያለበለዚያ ባልተወጣነው ግዴታ የመንገድ፣የጤና

ተቋማትና የትምህርት ቤት ግንባታ ጥያቄዎችን መጠየቅ አንችልም፡፡ ይህ ደግሞ የምንኖርበትን አካባቢ ኑሮ ያከብድብናል፡፡ ስለዚህ አንተም የሚጠበቅብህን ግብር በአግባቡ በመክፈል ግዴታህን ልትወጣ ይገባል፡፡"

"ልክ ብለሃል፡፡ በእውነት በዚህ መልኩ አስቤ አላውቅም፡፡ ከዚህ በኋላ ግን ግብር መክፈል ጥቅሙ ለሁላችንም መሆኑ ገብቶኛል፡፡ አንዲያውም አሁኑኑ ልሂድ፡፡ በል ደህና ዋል ወንድሜ፡፡" ብሎ ታደለ ምንዳን ተሰናብቶት እየተቻኮለ ወጣ፡፡

(ምንጭ፣ አዘጋጆቹ)

## ትምህርት ሁለት፡- በድምጽ የተቀረጹ የግብር ማስታወቂያዎች አዳምጦ ምላሽ መስጠት

መምህር/ት

በተመቾት መንገድ፣ በኤሌክትሮኒክስ (በስልክ፣በካሴት) የግብር ማስታወቂያዎችን ቀርጸው ወደ ክፍል በማምጣት ለተማሪዎች ያስደምጧቸው፡፡ በመቀጠል ባዳመጡት የግብር ማስታወቂያ መሰረት ጥያቄዎችን ያዘጋጁላቸውና ይጠይቋቸው፡፡ ለምላሻቸውም ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

# ለ መናገር

## ትምህርት ሦስት ፡- በምልልሶች በንቃት መሳተፍ

መምህር/ት፣

በዚህ ትምህርት ስር ተማሪዎች በሚና ጨዋታ እንዲሳተፉ ይጠበቃል፡፡ ሚና ጫወታ ተማሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች እንደመሆናቸው አፋቸውን በንግግር እንዲያፍታቱና በሰዎች ፊት መናገርን እንዲደፍሩ የሚያግዝ ጥሩ

የንግግር ማስተማሪያ ዘዴ መሆኑን ያስታውሱ፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መጽሐፍ በቀረቡት ከግብር መክፈል ጋር የተያያዙ የሚና ጨዋታዎች ሁለት ሁለት በመሆን በንቃት እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፡፡ በመጨረሻም አቀራረባቸውን ገምግመው ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

# ሐ ማንበብ

## ትምህርት አራት፡- የምንባብን ይዘት መተንተን

በዚህ ክፍል "ኮንትሮባንድ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች" በሚል ርዕስ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረበው ምንባብ ተማሪዎች በየግላቸው አንብበው ይዘቱን እንዲተነትኑ የቀረበ ነው፡፡ ከማንበባቸው በፊት የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ለመፈተሽና ለንባቡ ለማነቃቃት የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በእርስዎ መሪነት በቃል ይመልሱ፡፡ በማስከተል በማንበብ ሂደት የሚመለሰውን ጥያቄ መልሰው ንባባቸውን እንዲቀጥሉ ያድርጉ፡፡ ንባባቸውን ሲያጠናቅቁም የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በቃል ይመልሱ፡፡ እርስዎም ከምላሻቸው በመነሳት ግብረ መልስ ሰጥተው ትምህርቱን ያጠናቁ፡፡

# መ መጻፍ

## ትምህርት አምስት፡- አንቀጽ መጻፍ

መምህር/ት፣

በዚህ ክፍል ተማሪዎች አጠር ያለ አንቀጽ የመጻፍ ተግባር እንዲያከናውኑ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መጽሐፉ በቀረበው መሰረት መጀመሪያ ተማሪዎች በአካባቢያቸው ስለ ግብር አከፋፈል ልምድ አጠያይቀው አንድ አንቀጽ ጽፈው እንዲያመጡ የቤት ሥራ ይስጧቸው፡፡ ታሪኩን ጽፈው ሲመጡም ይመልከቱላቸውና አስተያየት ይስጧቸው፡፡

ቀጥሎም "አንቀጽ መጻፍ" በሚል በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረበውን አጭር ማስታወሻ መነሻ በማድረግ ስለ አንቀጽ ምንነትና በምክንያትና ውጤት አንቀጽን የማስፋፋት ስልት ያስረዱዋቸው፡፡ ከዚያም ቀደም ብለው ጽፈው የመጡትን ታሪክ ስለአንቀጽ አጻጻፍ በተማሩት መሰረት እንደገና አስተካክለው እንዲጽፉት ያድርጉ፡፡

በመጨረሻም በመረጡት ርዕስ በምክንያትና ውጤት የተስፋፋ አንድ አንቀጽ ጽፈው እንዲመጡ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡ ጽፈው ሲመለሱም ስራቸውን በማየት ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

# ሠ ቃላት

## ትምህርት ስድስት፡- ቃላትን በትክክል መጥራት

መምህር/ት፣

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ቃላትን በትክክል ስለ መጥራት ይማራሉ፡፡ ትምህርቱን ለመጀመር ተማሪዎች በተለያየ ቋንቋ አፍ የፈቱ እንደመሆናቸው አማርኛ ቋንቋን ሲናገሩ ለመጥራት ከሚያስቸግሯቸው ድምፆች የተወሰኑትን በማቅረብ በትክክል ለመጥራት እንዲሞክሩ በማድረግ ይጀምራል፡፡

ቀጥሎም በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ በማድረግ ቃላትን በትክክል ስለመጥራት ምንነትና አስፈላጊነት ያስረዷቸው፡፡ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ በክልላችን የሚገኙ ተማሪዎች ለመጥራት የሚያስቸግሯቸው ድምጾች እንደ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አይነት የተለያዩ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ስለዚህ እርሶዎም የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ለመጥራት የሚቸገሩባቸውን ድምፆች በመለየት በተለያዩ ቃላት ውስጥ እራስዎ እየጠሩ ሞዴል ሆነው በማሳየት በተደጋጋሚ ያለማምዷቸውና ለውጣቸውን ይገምግሙ፡፡

## 5.4. መርጃ መሳሪያ

- በድምፅ የተቀረጸ የግብር ማስታወቂያ (በስልክ ወይም በካሴት)
- እንደአካባቢው ጣልቃ እየገቡ የሚያስቸግሩ ድምጾች ያሉባቸውን ቃላት የሚያሳይ ሠንጠረዥ ናሙና አንቀጾች (ምልልሶች)

## 5.5. ግምገማ

- የተለያየ ድምጸት ያላቸውን ዐረፍተ ነገሮች አዳምጠው መለየታቸውን መገምገም፤
- በድምጽ የተቀረጹ የግብር ማስታወቂያዎችን አዳምጠው ምላሽ መስጠታቸውን መገምገም፤
- በምልልሶች በንቃት መሳተፋቸውን መከታተል፤
- ስለኮንትሮባንድ ያነበቡትን የምንባብ ይዘት መተንተን መቻላቸውን ማረጋገጥ፤
- አንቀጽ መጻፋቸውን ማረጋገጥ ፤
- ቃላትን በትክክለኛ አጠራራቸው (ንበታቸው) አስተካክለው መጥራታቸውን መከታተል።

# የሁለተኛው ወሰነ-ትምህርት

# ምዕራፍ ስድስት

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

(12 ክፍለ ጊዜያት)

## 6.1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች፣ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፦

- ምልክቶችን አይተው ከሚደመጡ ቃላዊ ገለጻዎች ጋር ያዛምዳሉ፤
- አዳምጠው የተረዱትን ይናገራሉ፤
- በሚና ጨዋታ ይሳተፋሉ፤
- በምንባብ የቀረቡ መመሪያዎችን አንብበው የተረዱትን ይገልጻሉ፤
- የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጽሑፎችን አንብበው ይዘቱን ይተነትናሉ ፤
- የጽህፈት ደረጃዎችን ይዘረዝራሉ፡፡
- የግጥም አነባበብ ስልትን ተከትለው ግጥም ያነባሉ፡፡

## 6.2. ከክፍለ ጊዜ ትምህርቶች የሚጠበቁ ውጤቶችና ዝርዝር ይዘቶች፡-

| የሚጠበቁ ውጤቶች | ዝርዝር ይዘቶች |
|---|---|
| ትምህርት አንድ፡-<br>• ምልክቶችን አይቶ ከሚደመጡ ቃላዊ ገለጻዎች ጋር ያዛምዳሉ፤ | • ምልክቶችን አይቶ ከሚደመጡ ቃላዊ ገለጻዎች ጋር ማዛመድ |
| ትምህርት ሁለት፡-<br>• አዳምጠው የተረዱትን ይናገራሉ፤ | • አዳምጠው የተረዱትን መናገር |
| ትምህርት ሦስት፡-<br>• በሚና ጨዋታ ይሳተፋሉ፤ | • በሚና ጨዋታ መሳተፍ |
| ትምህርት አራት፡-<br>• በምንባብ የቀረቡ መመሪያዎችን ይገልጻሉ፤ | • በምንባብ የቀረቡ መመሪያዎችን መግለጽ |
| ትምህርት አምስት፡-<br>• የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጽሁፎችን አንብበው ይዘታቸውን ይተነትናሉ፤ | • የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጽሑፎችን አንብቦ ይዘታቸውን መተንተን |
| ትምህርት ስድስት ፡-<br>• የጽህፈት ደረጃዎችን ይዘረዝራሉ፤ | • የጽህፈት ደረጃዎችን መዘርዘር |
| ትምህርት ሰባት፡-<br>• የግጥም አነባበብ ስልትን ተከትለው ግጥም ያነባሉ፡፡ | • ግጥም ማንበብ |

## 6.3. የትምህርቱ ይዘትና አቀራረብ

## ሀ ማዳመጥ

### ትምህርት አንድ፡- ምልክቶችን አይቶ ከሚደመጡ ቃላዊ ገለጻዎች ጋር ማዛመድ

**ተግባር**

መምህር/ት፣ በዚህ ክፍል ተማሪዎች ሳይንስና ቴክኖሎጂ ካበረከታቸው ትሩፋቶች አንዱ ስለሆነው የትራፊክ ምልክት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ትምህርቱ ከማዳመጥ ክሂል ጋር ተሳስሮ የቀረበ ነው፡፡ አተገባበሩም እርስዎ ስለምልክቶቹ ትርጉምና መልዕክት የሚያገኙ ከሆነ ከኢንተርኔት የሚገኙ የትራፊክ ምልክቶችን አይነትና ትርጉም በተመለከት የተዘጋጁ ቪዲዎችን ይጠቀሙ፡፡ ካልተቻለም ገለጻውን እራስዎ ያስደምጧቸው፡፡ ከማዳመጣቸው በፊት ግን የቀደመ እውቀታቸውን ለመቀስቀስ እንዲያግዝ የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በእርስዎ መሪነት ይመልሱ፡፡

በመማሪያ መጽሐፍ ተማሪዎች እንዲመለከቷቸው የቀረቡ የትራፊክ ምልክቶች ትርጉምና መልዕክት

| | |
|---|---|
| ሦስቱ የትራፊክ መብራቶች<br>አረንጓዴ- መኪና ማለፍ ይችላል<br>ቢጫ - በጥንቃቄ ሂድ<br>ቀይ - ቁም | መንገዱ ወደፊት የሚወስድና ወደግራ የሚታጠፍ ነው |
| የትምህርት ቤት አካባቢ በመሆኑ በጥንቃቄ ያሽከርክሩ | የእግረኛ ማቋረጫ ስለሆነ ቅድሚያ ይስጡ |
| ተሽከርካሪ ማቆም የተከለከለ ነው | መስቀለኛ መንገድ |

## ድህረ ማዳመጥ

መምህር/ት፣ በዚህ ክፍል ተማሪዎች በስዕሎቹ ከተመለከቷቸው የትራፊክ ምልክቶች ምን እንደተረዱ ይጠይቋቸው፡፡ በመቀጠል ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ተጨማሪ የትራፊክ ምልክቶች በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይሳሉላቸው፡፡ ከዚያም ስለምልክቶቹ መልዕክት ቃላዊ ገለጻ ይስጧቸውና ከተሳሉት ምልክቶች ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡ በመጨረሻም ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ሌሎች የትራፊክ ምልክቶችን መንገድ ላይ ተመልክተው ወይም አጠያይቀው በደብተራቸው ስለው እንዲያመጡ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡ ሲመለሱም ስራቸውን አይተው ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

በጥቁር ሰሌዳው ላይ እርስዎ እንዲስሉላቸው የቀረቡ ተጨማሪ የትራፊክ ምልክቶች

| | |
|---|---|
| የተሽከርካሪ ማቆሚያ | ቀጥ ያለ ዳገት ነውና ተጠንቀቁ |
| መንገዱ ወደቀኝና ወደ ፊት የሚያስኬድ ነው | የፍጥነት ገቺ ጉብታ አለ |
| መንገዱ ወደግራና ወደ ፊት የሚያስኬድ ነው | መንገዱ ወደፊት አይሄድም ግራና ቀኝ ታጠፉ |

## ትምህርት ሁለት፡- አዳምጠው የተረዱትን መናገር

**መምህር/ት፣**

ዓለም ሩጫ ላይ ነች እኛስ? በሚል ርዕስ ከዚህ በማስከተል የቀረበውን የማዳመጥ ምንባብ ድምፃዎን ከፍ አድርገው ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው፡፡ በቅድሚያ ግን ተማሪዎች የሚጠበቁባቸውን ውጤቶች እንዲያነቡ ጊዜ ይስጧቸው፡፡ ከዚያም

ምንባቡን ከማስደመጥዎ በፊት በእርስዎ መሪነት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡

በማዳመጥ ጊዜ በየመሀሉ ጥያቄዎች እየጠየቁ በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ ንባቡ ሲጠናቀቅ የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡

## ዓለም ሩጫ ላይ ነች እኛስ?

ዓለማችን አሁን ላይ ሳይንስና ተክኖሎጂን በመጠቀም ጫፍ ላይ የደረሰችበት ወቅት ነው፡፡ ጊዜው በራሪ ጀትና መንኮራኩሮች፣ ረጅም ርቀት በሰዓት የሚጓዙ ባቡሮች፣ረጅም ርቀት የሚወነጨፉ ሚሳየሎችና ኒዩክሌር መሳሪያዎች የተፈበረኩበት ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፣ ረጃጅም የባህር ላይ፣ የባህር ውስጥና የተራራ ውስጥ ድልድዮች እንዲሁም ረጃጅም የህንፃ ግንባታ ጥበቦች ሌላም ብዙ አዳዲስ ነገሮች እየታየባት ነው፡፡

በመጭዎቹ ቅርብ አመታት አሁን ካለው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጥበብ በተለየ፣ ላቅ ያሉ ፈጠራዎች ተግባራዊ እንደሚሆኑ የተለያዩ ሚዲያዎች በተጨባጭ መረጃ ያስቀምጣሉ፡፡ ሚዲያዎቹ በቅርቡ ነዳጅ የማይጠቀሙ በመብራትና በታዳሽ ሃይል የሚሰሩ ቴክኖሎጂዎች ተግባራዊ እንደሚደረጉ ይጠቁማሉ፡፡ ይህ የሃይል አጠቃቀም አለማችንን ከብክለት የፀዳች ያደርጋታል፤ እንዲሁም ዋጋው እየናረ የሄደውን የነዳጅ አቅርቦት ችግር ይፈታል፡፡ ጊዜው በህዋ ላይ ወይም በሌሎች ፕላኔቶች የሰው ልጅ እና ሌሎች ሕይወት ያላቸው ነገሮች የሚኖሩበትን ተጨማሪ ዓለም ለመፍጠር ከፍተኛ ውድድር የሚደረግበት ወቅት ነው፡፡

ሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዳሁኑ ዘመናዊነትን ሳይላበስና ልዩ ትኩረት ሳይሰጠው ጥንታዊ የሃገራችን ህዝቦች ሲጠቀሙት እንደነበር ታሪክ ይናገራል፡፡ በተለይም በከዋክብት ጥናት፣ በስነ-ህዋ ምርምር፣ በሂሳብ፣ በስነ-ህንፃ ግንባታ፣ ፊደላትን

በጽሑፍ አቀናጅቶ መጻፍ (የድንጋይ ላይ ጽሑፍ እንዲሁም የብራና ጽሑፍ) የመሳሰሉት ሰፊ ልምድ ያላቸውና ሲሰራባቸው የቆዩ ስልጣኔዎች ናቸው። ጥንታዊ ኢትዮጵያውያን አሁን ዓለም እየተጠቀመበት ያለውን ሳይንስና ቴክኖሎጂ በቀዳሚነት የፈጠሩ መሆናቸውን በርካታ ተመራማሪዎች ይጠቁማሉ።

ሀገራችን ኢትዮጵያ የቀደምት ስልጣኔ ምንጭ ብትሆንም አሁን ላይ ግን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ኋላቀር ከሚባሉት ሃገሮች ተርታ የምትሰለፍ ሀገር ሆናለች። ለዚህም እንደትልቅ ችግር የሚወሰደው ለሳይንስና ቴክኖሎጂ የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆን ነው። ኢትዮጵያ በፈጣን ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ለውጦች ላይ እንደመገኘቷ፣ቴክኖሎጂ ለዓለም እያበረከተ ያለውን ከፍተኛ አስተዋፅዖ እየተመለከቱ በዝምታ ማለፍ አዋጭ አይሆንም። ስለዚህ በቴክኖሎጂ በመታገዝ አሠራርን ማዘመን፣ ማቀላጠፍና ወጪ ቆጣቢ ማድረግ አስፈላጊነቱ አያከራርርም።

(ምንጭ - የተለያዩ ድረ ገጾች)

# ለ መናገር

## ትምህርት ሦስት፦ በሚና ጫወታ መሳተፍ

መምህር/ት፣ በዚህ ክፍል ተማሪዎች ጥንድ ጥንድ እየሆኑ ሚና በመለየት በሚና ጨዋታ እንዲሳተፉ ይጠበቃል። የሚና ጨዋታው አላማ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በንግግር በመጠቀም አንደበታቸውን እንዲያፍታቱ መሆኑን ልብ ይበሉ። በተቻለ መጠን አንድና ሁለት ብቻ ሳይሆን በርከት ያሉ ጥንድ ተማሪዎች በሚና ጨዋታው እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው።

# ሐ ማንበብ

## ትምህርት አራት፡-በምንባብ የቀረቡ መመሪያዎችን አንብቦ መግለጽ

መምህር/ት፣

በዚህ ክፍል ተማሪዎች በንባብ የቀረቡ መመሪያዎችን አንብበው እንዲገልጹ ይጠበቃል፡፡ መመሪያዎቹን ከማንበባቸው በፊት ከእሳት አደጋ ስለመጠበቅ ልምዳቸውን እንዲናገሩ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በእርስዎ መሪነት በቃል ይመልሱ፡፡ በንባብ ሂደት ከአደጋ ስለመጠበቅ የቀረበውን መመሪያ እንዴት ሊተገብሩት እንደሚችሉ እያሰቡ እንዲያነቡ ይንገሯቸው፡፡ በመጨረሻም በድህረ ንባብ በቀረቡት ጥያቄዎች መሰረት በመመሪያ አንድ የቀረቡትን የጥንቃቄ መልዕክቶች እንዲዘረዝሩ ቀጥሎም በክፍል ውስጥ ሊያሳዩዋቸው የሚችሏቸውን ለምሳሌ፡- በብርድልብስ ነበልባል እሳትን ማጥፋት የተመቻቸውን መርጠው በተግባር እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡ መምህር በተግባር የተደገፈ ትምህርት ተማሪዎችን እንደሚያነቃቃ ተገንዝበው ተግባሩን በቸልታ አይለፉት፡፡

በመቀጠል በመመሪያ ሁለት የቀረቡትን የጥንቃቄ መልዕክቶች በተመለከተ አንብበው የተረዱትን እጅ በማውጣት እንዲናገሩ ይምሯቸው፡፡ በማስከተል መመሪያዎቹን በየዕለቱ በቤታቸው እራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ከአደጋ ለመጠበቅ እንዲጠቀሙበት ያሳስቧቸው፡፡ የዚህ ተግባር አስፈላጊነት ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚማሩት ትምህርት እዚያው የሚቀር ሳይሆን በየዕለት ሕይወታቸው ውስጥ ሊጠቀሙበት የሚገባ መሆኑን እንዲረዱ ነው፡፡

## ትምህርት አምስት፡- የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጽሑፎችን አንብቦ ይዘታቸውን መተንተን

መምህር/ት፣ በዚህ የትምህርት ክፍል ተማሪዎች የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጽሑፎችን አንብበው የተረዱትን እንዲናገሩ ይጠበቃል፡፡ የትምህርቱ ዓላማ በማንበብ ክሂል ውስጥ ተማሪዎች ዘመኑ ከደረሰባቸው አዳዲስ የቴክኖሎጂ ስራዎች ጋር እንዲተዋወቁ ማድረግ ነው፡፡ የምንባቡ ርዕስ "የኮምፒዩተር ዘመን እየመጣ ነው" የሚል ነው፡፡ ይዘቱ በሌሎች የሳይንስ ትምህርቶች ውስጥ የሚያገኙትና ተማሪዎቹ ወጣት ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ አዳዲስ ነገሮችን የማወቅ ጉጉት የሚፈጠርባቸው በመሆኑ ምንባቡን በተሻለ ተነሳሽነት ያነቡታል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ እርስዎም ይህንኑ ሁኔታ በቅድመ ንባብ ጊዜ በመንገር ተማሪዎችን ለንባቡ ያነቃቁዋቸው፡፡ የቀደመ ዕውቀታቸውን ለመፈተሽ የተሰጡትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችም በእርስዎ መሪነት ይመልሱ፡፡

የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን ተማሪዎች አንብበው በተረዱት መሰረት በዝርዝር እንዲመልሱ ያበረታቱዋቸው፡፡ ለመመለስ የከበዷቸውን ወደኋላ ተመልሰው ከምንባቡ ደጋግመው ይመልከቱ፡፡ ጥያቄ አንድና ሁለት በቀጥታ ከምንባቡ የሚመለሱ በመሆናቸው ተማሪዎችም ከምንባቡ ባገኙት መረጃ መሰረት ይመልሱ፡፡ ጥያቄ ሦስትና አራት ግን ከምንባቡ ያገኙን ዕውቀት ከሕይወታቸው ጋር እንዲያዛምዱት የሚገፋፉ ናቸው፡፡ እርስዎም እነዚህ ተማሪዎች ነገ ይህቺን ሀገር የሚረከቡ ወጣቶች መሆናቸውን ልብ ይበሉ፡፡ ስለዚህ ለእነዚህ ዘመናዊ የቴክሎጂ አሰራሮች እራሳቸውን ባዕድ አድርገው እንዳያስቡ እንዲሁም ስለአዳዲስ አሰራሮች አስፈላጊነት እንዲያምኑና የእነሱ ድርሻ ምን መሆን እንዳለበት እንዲያስቡ ያበረታቷቸው፡፡

## መ መጻፍ

### ትምህርት ስድስት፡- የጽህፈት ደረጃዎችን መዘርዘር

**መምህር/ት፣**

በዚህ የትምህርት ክፍል ማንኛውም ደራሲ የሚያልፍባቸው የፅህፈት ደረጃዎች ወይም ሂደቶች በትምህርትነት ቀርበዋል፡፡ ትምህርቱን ለማቅረብ እንዲያስችል ስለጽህፈት ደረጃዎች የሚገልጽ ማስታወሻ በተማሪው መጽሐፍ ላይ ቀርቧል፡፡ ማስታወሻውን መነሻ በማድረግ የራሶን ምሳሌዎች ይጨምሩ፡፡ ትምህርቱን ተማሪዎችን በጥያቄና መልስ እያሳተፉ በደንብ ያስረዷቸው፡፡ ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁም እድል ይስጧቸው፡፡ በማስከተል ስለጽህፈት ደረጃዎች የተማሩትን መሰረት በማድረግ የቀረቡትን ጥያቄዎች በእርስዎ መሪነት በቃል ይመልሱ፡፡

## ሠ ሥነ ጽሑፍ

### ትምህርት ሰባት፡- ግጥም ማንበብ

በዚህ ክፍል የቀረበው ግጥም ተማሪዎች  የግጥም አነባበብ ስልትን በመከተል እንዲያነቡት የቀረበ ነው፡፡ ግጥሙ እንዴት መነበብ እንዳለበት እርስዎ እያነበቡ ሞዴል ሆነው ያሳዩአቸው፡፡ ቀጥሎም ተማሪዎች የእርስዎን የአነባበብ ስልት ተከትለው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በየተራ እንዲያነቡ ዕድል ይስጧቸው፡፡ ተማሪዎችም በየተራ ሲያነቡ የሚያዳምጡ ተማሪዎች  ስለአነባበቡ ትክክለኛነት አስተያየት እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

## 6.4. መርጃ መሳሪያ

- የተለያዩ የትራፊክ ምልክቶችን የሚያሳዩ ምስሎች
- የተለያዩ መመሪያዎች ያሉባቸው ጽሑፎች
- ሞዴል አጫጭር ግጥሞች

## 6.5. ግምገማ

- ምልክቶችን አይቶ ከሚደመጥ ቃላዊ ገለጻዎች ጋር ማዛመድ መቻላቸውን መከታተል፤
- በታቀደ የሚና ጫወታ በንቃት መሳተፋቸውን መከታተል፤
- በንባብ የቀረቡ መመሪያዎችን መተግበር መቻላቸውን ማጣራት፤
- የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጽሑፎች አንብበው ይዘታቸውን መተንተናቸውን በጥያቄ መፈተሽ፤
- የጽህፈት ደረጃዎችን መዘርዘራቸውን መከታተል።

# ምዕራፍ ሰባት

# ልዩ ፍላጎት

(10 ክፍለ ጊዜያት)

## 7.1. የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

ተማሪዎች፣ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ባዳመጡት መሰረት ክፍት ቦታዎችን ያሟላሉ፤
- በልዩ ፍላጎት ላይ ያተኮሩ ጉዳዮችን አዳምጠው ይወያያሉ፤
- በሚና ጨወታ ውስጥ ይሳተፋሉ፤
- በአካቶ ትምህርት ላይ የቀረበውን ጽሑፍ አንብበው አስተያየት ይሰጣሉ፤
- በሕይወት ተሞክሮዎቻቸው ላይ ሰፋ ያለ አንቀጽ ይጽፋሉ፤
- የማመልከቻ ደብዳቤ ይጽፋሉ።

## 7.2. ከክፍለ ጊዜ ትምህርቶች የሚጠበቁ ውጤቶችና ዝርዝር ይዘቶች፡-

| የሚጠበቁ ውጤቶች | ዝርዝር ይዘቶች |
|---|---|
| ትምህርት አንድ፡-<br>• ባዳመጡት መሰረት ክፍት ቦታዎችን ያሟላሉ፤ | • ባዳመጣችሁት መሰረት ክፍት ቦታዎችን መሟላት |
| ትምህርት ሁለት፡-<br>• በሚና ጫወታ ይሳተፋሉ፤ | • በሚና ጫወታ መሳተፍ |
| ትምህርት ሦስት፡-<br>• በአካትቶ ትምህርት ላይ የቀረበውን ጽሑፍ አንብበው አስተያየት ይሰጣሉ፤ | • በአካቶ ትምህርት ላይ የቀረበውን ጽሑፍ አንብቦ አስተያየት መስጠት |
| ትምህርት አራት፡-<br>• አንቀጽ ይጽፋሉ፤ | • አንቀጽ መጻፍ |
| ትምህርት አምስት ፡-<br>• የማመልከቻ ደብዳቤ ይጽፋሉ፤ | • የማመልከቻ ደብዳቤ መጻፍ |

## 7.3. የትምህርቱ ይዘትና አቀራረብ

## ሀ ማዳመጥ

### ትምህርት አንድ፡- ባዳመጣችሁት መሰረት ክፍት ቦታዎችን ማሟላት

መምህር/ት፣

በዚህ ክፍል "አካል ጉዳተኝነት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ጽሑፍ በንባብ ያስደምጧቸው፡፡ ትምህርቱ አካል ጉዳተኝነትን በተመለከተ እንዲኖራቸው የተፈለገው ግንዛቤ ከማዳመጥ ክሂል ጋር ተቀናጅቶ የቀረበ ነው፡፡ ጽሑፉን በንባብ ከማስደመጥዎ በፊት የቀድሞ ዕውቀታቸውን ለመቀስቀስ የቀረቡትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች እርስዎ እየጠየቋቸው ይመልሱ፡፡ በንባብ ጊዜ ደግሞ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረበውን የተጓደለ ጽሑፍ እርስዎን እያዳመጡ አሟልተው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

ተማሪዎቹ ጽሑፉን ከማዳመጣቸው በፊት የተጓደለውን ሀሳብ የያዙትን አንቀጾች አንብበው ምን ዓይነት መረጃዎችን ለማሟላት ማዳመጥ እንዳለባቸው ዓላማችውን እንዲለዩ ጥያቄዎቹን የሚያነቡበትን ሰዓት ይስጧቸው፡፡

በድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች ጊዜ ተማሪዎች ያዳመጡትን መረጃ መሠረት በማድረግ እንዲመልሷቸው የቀረቡ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ከአንድ እስከ ሦስት የቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች በቀጥታ በማዳመጥ ካገኙት መረጃ የሚመልሷቸው ናቸው፡፡ እነዚህን ጥያቄዎች በእርስዎ መሪነት በቃል እንዲመልሷቸው ያድርጉ፡፡ ጥያቄ አራትና አምስት ግን ተማሪዎች ከማዳመጥ ያገኙትን ዕውቀት መነሻ በማድረግ ከራሳቸው ሕይወት ጋር እንዲያዛምዱና

አስተያየትና አቋማቸውን እንዲገልጹ የሚጋብዙ ናቸው፡፡ እርሶም ይህንኑ በመረዳት በጥያቄዎቹ መልሶች ላይ በንቃት እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡

## አካል ጉዳተኝነት

አካል ጉዳት ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆነ የሰውነት ክፍል ላይ በደረሰ እክል ምክንያት አካል ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ተግባርን ማከናወን ሲያቅተው የሚከሰት ገደብ ወይም ውስንነት ነው፡፡ ውስንነት በተመጣጠነ ምግብ እጥረት፣ በበሽታ፣በንጽህና ጉድለት፣በጎጂ ልማዳዊ ድርጊት፣በአደጋና በመሳሰሉት ምክንያቶች ሊመጣ ይችላል፡፡ አካል ጉዳተኝነት በዓይነቱ ብዙ ቢሆንም በሦስት ወገን መድቦ መመልከቱ ተገቢ እንደሆነ የመስኩ ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡ ቀዳሚው የስሜት ህዋሳት ውስንነት ነው፤በዚህ ሥር ዓይነስውርነት (በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ማየት አለመቻል) እና መስማት መሳን (በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የመስማት ችሎታን ማጣት) ይካተታሉ፡፡ ሁለተኛው የእንቅስቃሴ አካላት ጉዳት ነው፤ ይህ ጉዳት የጀርባ አጥንት እክልን፣የእጅና የእግር እንቅስቃሴ ውስንነት ስጋ ደዌን ጠቅልሎ ይይዛል፡፡ ሦስተኛው ከሰው ልጅ የአእምሮ አሰራርና የባህሪይ ሁኔታ ጋር የሚዛመደው የአእምሮ እድገት ውስንነት ነው፡፡ በአንድ ሰው ላይ ከአንድ በላይ የአካል ጉዳት ሊደርስ የሚችል ሲሆን ይህ ዓይነቱ ውስንነት ተደራራቢ የአካል ጉዳት በመባል ይጠራል፡፡

የአካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም የማህበረሰብ አባል ተቆጥረው የትኞቹም ሰብዓዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መብቶቻቸው ሊከበሩላቸው ይገባል፡፡ ብዙዎች የአካል ውስንነቶች በእርግጥ እነዚህን የማህበረሰብ ክፍሎች ከመማር ከመስራትና እራሳቸውን ከማስተዳደር የሚያግዱ አይደሉም፡፡ አካል ጉዳተኞች ውጤታማ እንዳይሆኑ የሚታገዱት በባህል ውስጥ ሥር በሰደዱ ኋላቀር አመለካከቶችና በአካባቢያዊ ጫናዎች ነው፡፡ በዘመድ፣በቤተሰብ፣በጓደኛ፣በትምህርት ቤት በጉርብትና በሥራ ቦታ፣ በትምህርት ቤት የሚደርስባቸው መገለል ከቆመና

አካባያዊ ሁኔታዎች ከተመቻቹላቸው እነዚህ ወገኖች በየትኛውም ዘርፍ ሙሉና ውጤታማ ተሳትፎ ማድረግ ይችላሉ፡፡

(ምንጭ፡- በኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን የተዘጋጀ፤ ሰኔ 2005)

# ለ መናገር

## ትምህርት ሁለት፡-በሚና ጨወታ መሳተፍ

በዚህ የትምህርት ክፍል ተማሪዎች በሚና ጨወታ በንቃት እንዲሳተፉ ይጠበቃል፡፡ በእርሶ መሪነት አምስት አባላት ያለው ቡድን እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡ በማስከተል በመማሪያ መጽሐፍ የቀረበውን የመነሻ ሀሳብ መሰረት በማድረግ ሚና ለይተው እንዲጫወቱ ያድርጓቸው፡፡ የመነሻ ሀሳቡ የተሰጠበት ምክንያት ተማሪዎች ባልተዘጋጁበት ድንገት በሚና ጨዋታ እንዲተውኑ ሲጠየቁ ወዲያው ሀሳብ አመንጭተው ለመተግበር ጊዜ ስለሚወሰወድባቸው እና ስለሚቸገሩ ነው፡፡ የሚና ጨዋታዎች በተደጋሚ ሲደረጉ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን በቋንቋው የመጠቀም ድፍረት እንደሚጨምሩና አንደበታቸውን ለማፍታታት እንደሚረዷቸው ተገንዝበው ተግባሩን ተከታትለው ያሰሩዋቸው፡፡

# ሐ ማንበብ

## ትምህር ሦስት፡- በአካቶ ትምህርት ላይ የቀረበውን ጽሑፍ አንብቦ አስተያየት መስጠት

መምህር/ት፣

በዚህ ክፍል በቀረበው ትምህርት ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የቀረበውን ጽሑፍ በግልና በዝምታ አንብበው የተረዱትን እንዲገልጹና የግል አስተያየታቸውን እንዲገልጹ ይጠበቃል፡፡ ጽሑፉን እንዲያነቡ ከማዘዝዎ በፊት

የቀደመ ዕውቀታቸውን ለመቀስቀስና ለንባብ እንዲነቃቁ ለማድረግ የተሰጡትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ለሁለት ደቂቃ ተወያይተው እንዲመልሱ ይምሯቸው፡፡ በንባብ መሀል እንዲመልሱ የቀረበውን ጥያቄም ቆም ብለው እንዲመልሱ ያሳስቧቸው፡፡

ጽሑፉን በዝምታ አንብበው ከጨረሱ በኋላ በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የቀረቡትን የድህረ ንባብ ጥያቄዎች በእርስዎ መሪነት እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ ከቀረቡት ጥያቄዎች የመጀመሪያዎቹ ሦስት ጥያቄዎች በቀጥታ አንብበው ከተረዱት በመነሳት የሚመልሱት ነው፡፡ ጥያቄ አራትና አምስት ግን የተማሪዎቹን የግል አስተያየት የሚጠይቅ ነው፡፡ እርሶም ይህንኑ በመረዳት ተማሪዎች ችግር ፈቺ በሆነ መንገድ መሆን አለበት ብለው የሚያስቡትን እንዲገልጹ ያበረታቱዋቸው፡፡

# መ መጻፍ

## ትምህርት አራት ፡- አንቀጽ መጻፍ

መምህር/ት፣ በዚህ የትምህርት ክፍል ተማሪዎች በምዕራፍ አራት ላይ ስለ አንቀጽ አጻጻፍ የተማሩትን በማስታወስ በአካባቢያቸው ስለሚያውቁት አንድ የአካል ጉዳተኛ ሰው አንድ አንቀጽ ጽፈው እንዲመጡ የቤት ሥራ ይስጧቸው፡፡ ጽፈው ሲመጡም የጻፉትን አንቀጽ አይተው ግብረመልስ ይስጧቸው ፡፡

## ትምህርት አምስት፡- የማመልከቻ ደብዳቤ

መምህር/ት፣ በዚህ የትምህርት ክፍል ተማሪዎች የማመልከቻ ደብዳቤ እንዲጽፉ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ለትምህርቱ ይረዳ ዘንድ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የተሰጠውን ማስታወሻ እንዲሁም የማመልከቻ ደብዳቤ ምሳሌ መነሻ በማድረግ ተማሪዎችን በጥያቄና መልስ እያሳተፉ ያስረዷቸው፡፡

በማስከተል የተማሩትን የማመልከቻ ደብዳቤ የአጻጻፍ ሥርዓት በመከተል በትምህርት ቤት ውስጥ ከሚገኙ ክበባት በአንዱ አባል ለመሆን ማመልከቻ ደብዳቤ ጽፈው ለእርስዎ ያሳዩ፡፡ እርስዎም በደብዳቤው በትክክል መጻፉን ገምግመው ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## 7.4. መርጃ መሳሪዎች

- ናሙና አንቀጾች
- ናሙና የማመልከቻ ደብዳቤ

## 7.5. ግምገማ

- ባዳመጡት መሠረት ክፍት ቦታዎችን ማሟላታቸውን ማረጋገጥ፤
- በሚና ጨወታ በንቃት መሳተፋቸውን መከታተል፤
- በአካቶ ትምህርት ላይ የቀረበውን ጽሑፍ አንብበው አስተያየት መስጠታቸውን መገምገም፤
- ስለአካል ጉዳተኝነት የጻፉትን አንቀጽ መገምገም፤
- የማመልከቻ ደብዳቤ አጻጻፍ ሥርዓትን በመከተል መጻፋቸውን ማረጋገጥ፡፡

## 7.6. ናሙና የጥያቄ መልሶች

ሀ. ማዳመጥ

ትምህርት አንድ

1. በተመጣጠነ ምግብ እጥረት፣ በሽታ፣ በንጽህና ጉድለት፣ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊት፣በአደጋና በመሳሰሉት ምክንያቶች ሊመጣ ይችላል፡፡
2. ሦስተኛው ከሰው ልጅ የአእምሮ አሰራርና የባህሪይ ሁኔታ ጋር የሚዛመደው **<u>የአእምሮ ውስንነት</u>** ነው፡፡

3. በአንድ ሰው ላይ ከአንድ በላይ የአካል ጉዳት ሊደርስ የሚችል ሲሆን ይህ ዓይነቱ ውስንነት **ተደራራቢ የአካል ጉዳት** በመባል ይጠራል፡፡
4. የአካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም የማህበረሰብ አባል ተቆጥረው የትኛውም **ሰብዓዊ**፣ **ማህበራዊ** እና **ኢኮኖሚያዊ** መብቶቻቸው፣ ሊከበሩላቸው ይገባል፡፡
5. ብዙዎቹ የአካል ውስንነቶች በእርግጥ እነዚህን የማህበረሰብ ክፍሎች ከመማር **ከመስራት** እና እራሳቸውን ከማስተዳደር የሚያግዱ አይደሉም፡፡
6. የአካል ጉዳተኞች ውጤታማ እንዳይሆኑ የሚታገዱት **በባህል** ውስጥ ስር በሰደዱ ኋላ ቀር አመለካከቶችና በአካባቢ **ጫናዎች** ነው፡፡
7. በዘመድ፣ በቤተሰብ፣በጓደኛ፣ በጉርብትና፣በሥራ ቦታና በትምህርት ቤት የሚደርስባቸው **መገለል** ከቆመና ሁኔታዎች ከተመቻቹላቸው እነዚህ ወገኖች በየትኛውም ዘርፍ ሙሉና **ውጤታማ** ተሳትፎ ይኖራቸዋል፡፡

# ምዕራፍ ስምንት

# ሱስና መዘዙ

(10 ክፍለ ጊዜያት)

## 8.1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች፤ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ሱስና መዘዙ የሚለውን ጽሑፍ አዳምጠው የተረዱትን  ይናገራሉ፤
- የሱስ መከላከያ ዘዴን በሚመለከት የባለሙያ ምክር አዳምጠው ይናገራሉ፤
- በተለያዩ ሀሳቦች ላይ ማጠቃለያ ሀሳብ ያፈልቃሉ፤
- በሱሰኝነት የሚያውቁትን  ሰው ታሪክ ይናገራሉ፤
- በተማሪዎች ፊት ክርክር ያደርጋሉ፤
- አንብበው በተረዱት መሰረት ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፤
- የሕይወት ታሪክ ይጽፋሉ፤
- ምሳሌያዊ ንግግሮችን ይጽፋሉ፡፡

## 8.2. ከክፍለ ጊዜ ትምህርቶች የሚጠበቁ ውጤቶችና ዝርዝር ይዘቶች፡-

| የሚጠበቁ ውጤቶች | ዝርዝር ይዘቶች |
|---|---|
| ትምህርት አንድ፡-<br>• አዳምጦ የጽሑፍን ፍሬ ነገር ይናገራሉ | • አዳምጦ የጽሑፍን ፍሬ ነገር መናገር |
| ትምህርት ሁለት፡-<br>• በማዳመጥ የተገኘ ሀሳብን ያጠቃልላሉ፤ ታሪክ ይናገራሉ፤ | • በማዳመጥ የተገኘ ሀሳብን ማጠቃለልና ታሪክ መናገር |
| ትምህርት ሦስት፡-<br>• ክርክር ያቀርባሉ፤ | • ክርክር ማዘጋጀትና አቀራረብ |
| ትምህርት አራት፡-<br>• አንብበው የተረዱትን ይናገራሉ፤ | • አንብቦ መረዳት |
| ትምህርት አምስት ፡-<br>• የሕይወት ታሪክ ይጽፋሉ፤ | • የሕይወት ታሪክ መጻፍ |
| ትምህርት ስድስት፡-<br>• ምሳሌያዊ ንግግሮችን ይጽፋሉ፡፡ | • ምሳሌያዊ ንግግሮችን መጻፍ |

## 8.3. የትምህርቱ ይዘትና አቀራረብ

## ሀ ማዳመጥ

### ትምህርት አንድ፡- አዳምጦ የጽሑፍን ፍሬ ነገር መናገር

መምህር/ት፣

በዚህ ክፍል "ሱስና መዘዙ" በሚል ርዕስ የቀረበው ጽሑፍ የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ለማሳደግና ለመመዘን ታስቦ የቀረበ በመሆኑ እርስዎ ያንብቡላቸው፡፡ ከማዳመጣቸው በፊት ግን ሱስን በተመለከተ ያላቸውን የቀደመ ዕውቀት ለመቀስቀስ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረቡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች  በእርስዎ መሪነት እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡ በማዳመጥ ሂደት በየታሪኩ መሀል የታሪኩ ባለቤት ቀጥሎ ምን ሊያጋጥመው እንደሚችል ይጠቁሟቸው፡፡

በድህረ ማዳመጥ ክፍል የቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች ያዳመጡትን ታሪክ መሠረት በማድረግ የሚመልሷቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም በእርሶ መሪነት ጥያቄዎቹን በቃል እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡

## ሱስና መዘዙ

አቶ ደሰኖ በአንድ የገጠር መንደር ነዋሪ ሲሆን ባለትዳርና የአራት ልጆች አባት ነው፡፡ የሚተዳደረው በአህያ ጋሪ የተለያዩ ጭነቶችን በመጫን ገበያ ወዳለበት ሥፍራ በማድረስ በሚከፈለው ገንዘብ ነው፡፡ ደሰኖ ቀን ቀን ሥራ ውሎ ደክሞ ያጠራቀመውን ገንዘብ በየአረቄ ቤቱ እየበተነ ምሽት ወደ ቤት ሲገባ ሚስትና ልጆቹን በየእለቱ ይደበድባል፡፡ በዚህ ምክንያት የተማረረችው የልጅነት ሚስቱ ልጆቹን ጥላበት ወደ ቤተሰቦቿ ከሄደች ቀናት ተቆጠሩ፡፡

ደሰኖ መጠጥ አዘውታሪነቱ እየተባባሰ ሲመጣ በጠዋት ተነስቶ ሥራውን በአግባቡ መወጣት አቃተው፡፡ በዚህ ምክንያት ጓደኞቹ ጋሪውን እንዲነዱለት በመስጠት የሚያመጡለትን ገንዘብ ለሲጋራና ለአረቄ ማድረጉንንና ጓደኞቹን መጋበዙን ተያያዘው፡፡

ከዕለታት በአንዱ ቀን እንደተለመደው ማታ ሰክሮ አምሽቶ ወደ ቤቱ ሲገባ የገቢ ምንጩ የሆነው አህያ ጋሪ ከመኪና ጋር ተጋጭቶ ከጥቅም ውጪ መሆኑን ሰማ፡፡ ከንብረቱ መውደም በኋላ ደሰኖ ሕይወት እጅጉን ፈታኝ ሆነበት፡፡ ትላንት ለማንም ሲበትን የነበረው ገንዘብ ዛሬ የሚበላው እስኪያጣ ቸገረው፡፡ ልጆቹንም መግቦ ማኖር አቃተው፡፡ ከቤተሰቦቹ በውርስ ያገኘውን መሬት ሸጦ ገንዘብ ለማግኘት ቢሞክርም በሱሱ ምክንያት ገንዘቡ ብዙም ሳይቆይ አለቀ፡፡

አንድ ሁለት ጊዜ በቀን ሰራተኝነት የተለያዩ የጉልበት ሥራዎችን ለመስራት ቢሞክርም በራሱ ንብረት እንደፈለገ ማዘዝ ስለለመደ ተቀጣሪ መሆንን ሊለምደው አልቻለም፡፡ በተለይ ማታ አረቄ ጠጥቶ አምሽቶ ስለሚገባ ጠዋት ተነስቶ መደበኛ ሥራውን መስራት አቃተው፡፡ እያደር ሱሰኛ መሆኑንና በጠዋት አለመነሳቱን የሰሙ ሰዎች ለምንም ሥራ ሊቀጥሩት አልፈለጉም፡፡

ደሰኖ ኑሮ ከበደው፤ ሱሱም ተባባሰበት፡፡ ከሚያውቃቸው ሰዎች ጫትና ሲጋራ መግዣ ሳንቲም እየለመነ ያለምንም ሥራ በየሰፈሩ ማውደልደል ጀመረ፡፡ በመጨረሻም የአልኮል መጠጥ ለረጅም ጊዜ በመውሰዱ ምክንያት ጉበቱ ስለተጎዳ በጸና ታሞ ሕይወቱ አለፈ፤ልጆቹም ያለአሳዳጊ ተበተኑ፡፡ ደሰኖ ሱስ ባመጣበት መዘዝ ሕይወቱንም ቤተሰቡንም አጣ፡፡

(ምንጭ፡- ከአዘጋጆቹ)

በተግባር ሁለት ከሱስ ለመላቀቅ የሚያግዙ፣ በባለሙያዎች ዘወትር የሚመከሩ ዘዴዎች ቀርበዋል፡፡ ተማሪዎች እነዚህን ምክሮች አዳምጠው የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይመልሱ፡፡

**ከሱስ ለመላቀቅ የሚያግዙ፣ የባለሙያ ምክሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡**

1. አልኮል፣ ጫትና ሌሎች ዕጾችን ልናገኝ የምንችልባቸውን ሁኔታዎች ማስወገድ፣
2. አልኮል፣ ጫትና ሌሎች ዕጾችን የመጠቀም ስሜት በሚያይልበት ጊዜ ከጓደኞች ጋር ጊዜ ማሳለፍ፣ ሙዚቃ ማዳመጥ ወይም ሌሎች ስሜቱን በሚያስረሱ ሁኔታዎች ራስን ማጥመድ፣
3. የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ፣
4. በጉዳዩ ላይ ከቤተሰብና ጓደኛ ጋር በመወያየት እገዛ ማግኘት፣
5. ጤነኛ የአመጋገብ ሥርዓት ማዳበር ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎች ዘዴዎችን ተጠቅሞ ከሱስ መላቀቅ  ካልተቻለ ወደ ህክምና ቦታ በመሄድ የባለሙያ ድጋፍ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

# ለ መናገር

## ትምህርት ሁለት፡- በማዳመጥ የተገኘ ሀሳብን ማጠቃለልና ታሪኩን መናገር

መምህር/ት፣ በዚህ የትምህርት ክፍል ተማሪዎች በተለያዩ ሀሳቦች ላይ ማጠቃለያ እንዲያፈልቁ ይጠበቃል፡፡ በዚህም መሠረት ቀደም ሲል በነበረው የማዳመጥ ክፍለ ትምህርት ሱስና መዘዙ በሚል ርዕስ ያዳመጡትን ታሪክ ሀሳብ አጠቃለው በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ በማስከተልም በሁለተኛው ተግባር በተገለጸው መሠረት በአካባቢያቸው በሱሰኝነቱ የሚያውቁትን ሰው ታሪክ ለክፍል ጓደኞቻቸው ይናገሩ፡፡

የተቀሩት ተማሪዎች ደግሞ ከጓደኞቻቸው ያዳመጡትን ታሪክ እጅ በማውጣት ጠቅለል አድርገው ይናገሩ፡፡

## ትምህርት ሦስት-፡ የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ

በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች በክፍል ተማሪዎች ፊት ክርክር እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡ ክርክር ተማሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች እንደመሆናቸው መጠን የሀሳብ አፍልቆታቸውን ለማቀላጠፍና በሰዎች ፊት የመናገር ልምዳቸውን ለማዳበር በጣም ጠቃሚ የንግግር ማስተማሪያ ዘዴ መሆኑን ልብ ይበሉ፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ ስለክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ የቀረበው ማስታወሻ ስለትምህርቱ ግንዛቤ ስለሚፈጥርላቸው  በቅድሚያ ያስረዷቸው፡፡

ትምህርቱ ከተጠናቀቀ በኋላ አምስት አባላት ያሉት ቡድን በእርስዎ መሪነት ይመስርቱ፡፡ ከአምስቱ አባላት አንዱ ዳኛ ሆኖ እንዲሰየምና የቀሩት ሁለት ሁለት ተማሪዎች በተቃራኒ ሀሳብ ጎራ ተሰልፈው ለመከራከር እንዲዘጋጁ ይንገሯቸው፡፡ ከዚያም ለክርክር የሚመቹ የተወሰኑ ርዕሶችን ይስጡና  ከተሰጡት ርዕሶች ተማሪዎች የፈለጉትን በመውሰድ በቤታቸው ተዘጋጅተው እንዲመጡ የቤት ሥራ ይስጧቸው፡፡ ሰርተው ሲመለሱም ለእያንዳንዱ ቡድን ሰዓት መድበው በመስጠት በየተራ ክርክሩን እንዲያካሂዱ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም ለሰሩት ሥራ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

# ሐ ማንበብ

## ትምህርት አራት፡- አንብቦ መረዳት

መምህር/ት፣ በዚህ የትምህርት ክፍል "ሱስና ሱሰኝነት" በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ተማሪዎች በግልና በዝምታ የሚያነቡት ነው፡፡ ከማንበባቸው በፊት ሱስና ሱሰኝነትን አስመልክቶ ያላቸውን የቀደመ ዕውቀት ለመፈተሽ የቀረቡትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ በንባብ ጊዜ የቀረቡ ጥያቄዎች በንባብ መሀል የሚመለሱ ናቸው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ይህንኑ አውቀው እራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ይንገሯቸው፡፡ በመጨረሻም ባነበቡት መሠረት የሚመልሷቸውን የድህረ ንባብ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

በምንባቡ መጀመሪያ ላይ ያለውን ስዕል በማየት ተማሪዎች ስለምን ሊያነቡ እንደሆነ እንዲገምቱ ይጠይቋቸው፡፡

# መ መጻፍ

## ትምህርት አምስት፡- የሕይወት ታሪክ መጻፍ

መምህር/ት፣

በዚህ የትምህርት ክፍል ተማሪዎች የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ መመሪያን ተከትለው የሕይወት ታሪክ እንዲጽፉ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መጽሐፋቸው የቀረበውን ማስታወሻ ያስረዷቸውና በቀረበው የግለሰብ (የሌላ ሰው) የሕይወት ታሪክ ምሳሌ መሰረት የራሳቸውን የሕይወት ታሪክ ጽፈው በማምጣት እጅ በማውጣት ለክፍል ጓደኞቻቸው በቃል ያቅርቡ፡፡

# ሠ ሥነ ጽሑፍ

## ትምህርት ስድስት፡- ምሳሌያዊ ንግግሮች

በዚህ ክፍል ተማሪዎች የምሳሌያዊ ንግግሮችን ምንነት እንዲያውቁና እንዲጽፉ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም የቀደመ ዕውቀታቸውን ለመፈተሽ በቃል እንዲመልሱ የቀረቡትን ጥያቄዎች በማስቀደም ተማሪዎችን ባሳተፈ መልኩ ስለትምህርቱ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ በመጨረሻም የምሳሌያዊ አነጋገሮችን መልዕክት እንዲጽፉና ጅምር ምሳሌያዊ ንግግሮችን እንዲያሟሉ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ያድረጉና ስለትክክለኛነቱ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## 8.4. መርጃ መሳሪያ

- ለናሙና የተጻፉ የሕይወት ታሪኮች
- የተለያዩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን የያዘ ቻርት

## 8.5. ግምገማ

- አዳምጦ የጽሑፉን ፍሬ ነገር መናገራቸውን መከታተል
- በማዳመጥ የተገኘ ሀሳብ ማጠቃለላቸውንና ታሪክ መናገራቸውን መከታተል
- ስለሱሰኝነት የቀረበውን ምንባብ አንብበው መረዳታቸውን በጥያቄ መፈተሽ
- የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ መመሪያን ተከትለው የሕይወት ታሪክ መጻፋቸውን መገምገም

## 8.6 ናሙና መልሶች

### ትምህርት ስድስት

2 ሀ. ሠርግ በጭብጨባ

ለ. በርበሬ ቀንጥሱ

ሐ. ማን ያርዳ የቀበረ

መ. እንጀራ ያለወጥ

ሠ. ሲሮጡ ይፈታል

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# ሀገር በቀል ዕውቀቶች

(12 ክፍለ ጊዜያት)

## 9.1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች፣ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ያዳመጡትን ሀገር በቀል ዕውቀት መሠረት በማድረግ ልምድ ይለዋወጣሉ፤
- ስለሀገር በቀል ዕውቀት አንብበው የተረዱትን ይናገራሉ፤
- በተለያዩ ማህበራዊ ዐውዶች ውስጥ በሚታዩ የንግግርና የሰላምታ አቀራረብ ሁኔታዎች ላይ ልምድ ይለዋወጣሉ፤
- ድርሰት ይጽፋሉ፤
- በጠንካራ ሰራተኛነት ባህል ላይ ትኩረት ያደረገ ጽሑፍ ይጽፋሉ፤
- የተረቶችን ዋና ሀሳብ ይናገራሉ፤
- አፈ ታሪኮችን ይናገራሉ።

## 9.2. ከክፍለ ጊዜ ትምህርቶች የሚጠበቁ ውጤቶችና ዝርዝር ይዘቶች፡-

| የሚጠበቁ ውጤቶች | ዝርዝር ይዘቶች |
|---|---|
| ትምህርት አንድ፡- <br>• ባዳመጡት ሀገር በቀል ዕውቀት መሰረት ልምድ ይለዋወጣሉ፤ | • ባዳመጡት ሀገር በቀል ዕውቀት መሰረት ልምድ መለዋወጥ |
| ትምህርት ሁለት፡- <br>• ስለሀገር በቀል ዕውቀት አንብበው የተረዱትን ይናገራሉ፤ | • ስለሀገር በቀል ዕውቀት አንብበው የተረዱትን መናገር |
| ትምህርት ሦስት፡- <br>• በተለያዩ ማህበራዊ ዐውዶች ውስጥ ይናገራሉ፤ | • በተለያዩ ማህበራዊ ዐውዶች ውስጥ መናገር |
| ትምህርት አራት፡- <br>• ድርሰት ይጽፋሉ፡፡ | • ድርሰት መጻፍ |
| ትምህርት አምስት፡- <br>የተረቶችን ዋና ሀሳብ ይጽፋሉ | • ተረቶችን መጻፍ |
| ትምህርት ስድስት፡- <br>አፈ ታሪኮችን ይናገራሉ | • አፈ ታሪኮችን መናገር |

## 9.3. የትምህርቱ ይዘትና አቀራረብ

## ሀ ማዳመጥ

### ትምህርት አንድ፡- ባዳመጡት ሀገር በቀል ዕውቀት መሠረት ልምድ መለዋወጥ

መምህር/ት ተማሪዎችዎ በቅድሚያ የሚጠበቁባቸውን ውጤቶች ያንብቡ፡፡ **"የዲዚ ብሔረሰብ ባህላዊ ዳኝነት"** በሚል ርዕስ በመምህሩ መምሪያ የቀረበው ጽሑፍ የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ለማሳደግና ባዳመጡት መሠረት ልምድ የመለዋወጥ ክህሎታቸውን ለመገምገም የቀረበ ነው፡፡ ፍቃደኛ የሆኑ ሁለት ተማሪዎችን በየተራ በማስነሳት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ የክፍሉ ተማሪዎችም በጥሞና እንዲያዳምጡ ያድርጉ፡፡ ከዚያ በፊት ግን በቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ላይ በእርስዎ መሪነት ይነጋገሩ፡፡ የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዳሉባቸው በመጠቆም ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ አሳስበው ወደ ንባቡ ይለፉ፡፡ ንባቡ ሲጠናቀቅ የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይመልሱ፡፡ ጥያቄዎቹ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በስፋት እንዲገልጹ የሚጋብዙ ስለሆኑ ለውይይት ሰፋ ያለ ጊዜ ይስጧቸው፡፡

## የዲዚ ብሔረሰብ ባህላዊ ዳኝነት

የዲዚ ብሔረሰብ በደቡብ ክልል የሚገኝ ማህበረሰብ ነው፡፡ በክልሉ የሚገኙ ሌሎች ማህበረሰቦች ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀሙባቸው ባህላዊ መንገዶች እንዳሏቸው ሁሉ የዲዚ ብሔረሰብም የራሱ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች አሉት፡፡ ግጭት ሲከሰት እንደ ጉዳዩ ክብደትና ቅለት ከሽማግሌዎች አንስቶ እስከ ጎሳ መሪዎች ውሳኔ ሊሰጡበት ይችላሉ፡፡ በባህሉ ከሚዳኙ ጉዳዮች መካከል የእርስ በእርስ ግጭት (ጥል)፣ ሌብነትና አስገድዶ መድፈር የመሳሰሉት ናቸው፡፡

በብሔረሰቡ ባህል እነዚህን እና ሌሎች ጥፋቶች መፈፀም በትንሹ ከብት ከመክፈል ጀምሮ በግርፋት እንዲሁም በሞት ሊያስቀጣ እንደሚችል ይነገራል፡፡ ለውሳኔዎች እንደ ህግ የሚያገለግለው ባህሉ ሲሆን ተቀጪዎቹ ከብሔረሰቡ ባህል ወግና ልማድ ማፈንገጥ ተገቢ አለመሆኑን እንዲማሩ የሚያስችል የዳኝነት ሥርዓት ነው፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች በሁለት ጎሳዎች መካከል የከረረ ግጭት ከተፈጠረ ሌሎች ጎሳዎች እርቅ እንዲፈጠር በመሀል በመግባት በአንደኛው ባላባት ወይም በታዋቂ ግለሰብ ግቢ ውስጥ በማደራደር የማስታረቅ/የዳኝነት ሥራ ይሰራሉ፡፡ በድርድሩ መሠረት ከስምምነት ላይ ከተደረሰ በኋላ ጥፋተኛው ወገን በሬ/ወይፈን በቅጣት መልክ እንዲያቀርብ ይደረግና የበሬው ወይም የወይፈኑ ስጋ ተጠብሶ በአንድ ማዕድ ሁለቱም እንዲቀምሱት በማድረግ የእርቅ ሥርዓቱ ይጠናቀቃል፡፡

ከተፈጠረው ግጭት የተነሳ ነፍስ መጥፋት ቢከሰት የገዳዩና የሟች ወገኖችን በማቀራረብ የማስታረቅ እና ባህላዊ የእርቅ ሥርዓቶችን የመፈፀም ስራ ይከናወናል፡፡ ጉዳዩ በሽማግሌዎች ከተመረመረ በኋላ ደም ለማድረቅና በቂም በቀል እንዳይፈላለጉ ለማድረግ ሙዳ ስጋ በሁለት ጫፍ ነክሰው በመያዝ እንዲበሉና በጦር መሳሪያ ላይ ተረማምደው እንዲያልፉ ይደረጋል፡፡ እነዚህ ባህላዊ ሥርዓቶች ከተፈፀሙ የተከሰተው ደም መፍሰስ ተወግዷል ተብሎ ይታመናል፡፡ ሥርዓቱም በባህሉ “በትኩስ ወተት መታጠብ” የሚል ስያሜ አለው፡፡

(ምንጭ፣ደስታ ወልደመስቀል፣2006)

# ለ ማንበብ

## ትምህርት ሁለት፡- ስለሀገር በቀል ዕውቀት አንብበው የተረዱትን መናገር

መምህር/ት፣ በዚህ ክፍል የማንበብ ክሂል ከመናገር ክሂል ጋር ተቀናጅቶ ቀርቧል፡፡ የቀረበውን ጽሑፍ ተማሪዎች በየግላቸው በዝምታ እንዲያነቡት ይምከሯቸው፡፡ ከማንበባቸው በፊትም የቀደመ ዕውቀታቸውን ለመፈተሽ እና ለንባቡ ለማነቃቃት የቀረቡትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በቃል ይመልሱ፡፡ በንባብ ጊዜም ንባባቸውን ገታ አድርገው እንዲመልሱ የቀረበውን ጥያቄ እንዲመልሱ ያሳስቧቸው፡፡ ንባቡ ሲጠናቀቅ የድህረ ንባብ ጥያቄዎች ላይ በቡድን እየተወያዩ ይመልሱ፡፡ በመጨረሻም የተወያዩባቸውን ሀሳቦች እጅ በማውጣት እንዲመልሱ ይጠይቋቸው፡፡

# ሐ መናገር

## ትምህርት ሦስት፡- በተለያዩ ማህበራዊ ዐውዶች ውስጥ መናገር

በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በተለያዩ ማህበራዊ ዐውዶች ውስጥ ቋንቋውን እንዴት እንደሚጠቀሙ አውቀው እንዲለማመዱት ይጠበቃል፡፡ እርስዎም ይህንኑ በመረዳት መጀመሪያ በራሳቸው ቋንቋ በእነዚህ ማህበራዊ ዐውዶች ውስጥ የሚኖራቸውን የቋንቋ አጠቃቀም ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር ልምዳቸውን እንዲለዋወጡ ያድርጓቸው፡፡ በማስከተል የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በእነዚህ ዐውዶች ውስጥ የቋንቋ አጠቃቀማቸውን እርስዎ እየተናገሩ ያሳዩዋቸው፡፡ ቀጥሎ ከእርስዎ ባዩት መሰረት በዐውዱ ውስጥ እንዳሉ ሆነው እንዲለማመዱ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፡፡

## መ መጻፍ

### ትምህርት አራት፡- ድርሰት መጻፍ

በዚህ ክፍል በስፋት የሚታወቁትን አራት የድርሰት ዓይነቶች እንዲለዩና በሙከራ ደረጃ አስረጅ ድርሰትን በእርስዎ መሪነት መጻፍ እንዲለማመዱ ይጠበቃል፡፡ የጠንካራ ሰራተኝነት ባህል በመጻፍ ክሂል እንዲገለጽ ሆኖ ቀርቧል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎችዎ በእርስዎ መሪነት ቡድን መስርተው "ጠንካራ የስራ ባህል" በሚል ርዕስ የቀረበውን አጭር ገላጭ ድርሰት እንዴት እንደተጻፈ በትኩረት እንዲመለከቱ ያድርጓቸው፡፡ ይህንን የአጻጻፍ ሥርዓት በመከተል በአካባቢያቸው በጠንካራ ሰራተኝነቱ አርአያ የሆነ አንድ ሰው እንዲመርጡና ሦስት አንቀጽ ያለው ገላጭ ድርሰት እቤታችሁ ጽፈው እንዲመጡ ይንገሯቸው፡፡ ጽፈው ሲመለሱም ድርሰታቸውን ሰብስበው በመገምገም የጽሑፍ አስተያየት ይስጧቸው፡፡

## ሠ ሥነ ጽሑፍ

### ትምህርት አምስት፡- የተረቶችን ዋና ሀሳብ መናገር

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ተረት አንብበው ዋና ሀሳቡን እንዲናገሩ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም የቀደመ ዕውቀታቸውን በመጠቀም እንዲመልሱ የቀረበውን ጥያቄ በመጠየቅ ትምህርቱን ይጀምሩ፡፡ በማስከተልም በማስታወሻው ክፍል ተረትን አስመልክቶ የተሰጠውን ገለጻ አንብበው እንዲረዱት ጊዜ ይስጧቸው፡፡ ከዚያም ምን እንደተረዱ ይጠይቋቸውና ከሚያውቁት በመነሳት የማያውቁትን ይንገሯቸው፡፡ በመጨረሻም በምሳሌነት የቀረበውን ተረት አንብበው መልዕክቱን እንዲናገሩ ያድርጉና ተረት አጠያይቀው በማምጣት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

## ትምህርት ስድስት፡- አፈ ታሪኮችን መናገር

በዚህ ክፍል ተማሪዎች አፈ ታሪኮችን እንዲናገሩ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ስለአፈ ታሪክ የሚያውቁትን በመጠየቅ በማስታወሻ ክፍል የቀረበውን ገለጻ ተማሪዎችን በንቃት በማሳተፍ ያስረዷቸው፡፡ በመቀጠል በምሳሌነት የቀረበውን ስለአጼ ልብነ ድንግል የቀረበውን አፈ ታሪክ እንዲያነቡ ያድርጉና በአካባቢያቸው ከሚነገሩ አፈ ታሪኮች አንዱን አጠያይቀው በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

### 9.4 መርጃ መሳሪያ

- ናሙና ተረቶች
- ናሙና አፈ ታሪኮች

### 9.5 ግምገማ

- ባዳመጡት መሠረት ሀገር በቀል ዕውቀት መሠረት ልምድ መለዋወጣቸውን መከታተል፤
- ስለሀገር በቀል ዕውቀት አንብበው የተረዱትን መናገራቸውን መከታተል፤
- በተለያዩ ማህበራዊ ዐውዶች ውስጥ በተገቢ የቋንቋ አጠቃቀም መገልገላቸውን ማረጋገጥ፤
- የድርሰት ዓይነቶችን ለይተው ገላጭ/አስረጂ ድርሰት በአግባቡ መጻፋቸውን መገምገም፤
- የተረቶችን ዋና ሀሳብ መናገራቸውን መገምገም፤
- አፈ ታሪኮችን መናገራቸውን መከታተል፡፡

# ምዕራፍ አስር

# አጭር ልቦለድ

**(8 ክፍለ ጊዜያት)**

## 10.1.የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች፣ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- የንግግር ድምጸቶችን አዳምጠው ይለማመዳሉ፤
- በራሳቸው ፍጥነት አጫጭር ልቦለዶችን ያነባሉ፤
- የልቦለድ አላባውያንን (ገጸ ባህርያትንና መቼትን) ይለያሉ፤

## 10.2. ከክፍለ ጊዜ ትምህርቶች የሚጠበቁ ውጤቶችና ዝርዝር

**ይዘቶች፡-**

| የሚጠበቁ ውጤቶች | ዝርዝር ይዘቶች |
|---|---|
| **ትምህርት አንድ፡-**<br>• የንግግር ድምጸቶችን አዳምጠው ይለያሉ፤ | • የንግግር ድምጸቶችን አዳምጦ መለየት |
| **ትምህርት ሁለት፡-**<br>• አጫጭር ልቦለዶችን ያነባሉ፤ | • አጫጭር ልቦለዶችን ማንበብ |
| **ትምህርት ሦስት፡-**<br>• የልቦለድ አላባውያንን ይለያሉ | • የልቦለድ አላባውያንን መለየት |

## 10.2. የትምህርቱ ይዘትና አቀራረብ

## ሀ ማዳመጥና መናገር

### ትምህርት አንድ ፡ የንግግር ድምጸቶችን አዳምጦ መለየት

*መምህር/ት፤*

በዚህ ክፍል ተማሪዎች በተለያዩ ዐውዶች የሚኖሩ የንግግር ድምጸቶችን አዳምጠው እንዲለዩ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የንግግር ድምፀትን በተመለከተ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ በማድረግ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡ የተሰጡትን ሦስት ዐውዶች ምሳሌ በማድረግ የንግግር ድምጸትን /የድምጽ ቃና ወይም የድምጽ ከፍታና ዝቅታን/ እንዲያጤኑ ያድርጉ፡፡ በመቀጠል ንግግሩ የቀረበበትን ስሜት እና የንግግሩን መንፈስ ለማስረዳት ይሞክሩ፡፡

እነዚህ የንግግር ድምጸቶች አንዳንዶቹ በጽሑፍ ውስጥ በሥርዓተ ነጥቦች እንደሚወከሉም ይንገሯቸው፡፡ በመቀጠልም በማስታወሻው ክፍል በቀረቡት ዐውዶች መሰረት ጥያቄዎቹን እንዲመልሱ ያድርጉና ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡ ቀጥሎም በመልመጃ ክፍል በሁለት የታገቱ ሰዎች መካከል የተደረገ ምልልስን በጥንድ ሆነው ድምጻቸውን በማሰማት እያነበቡ የጥያቄና የመገረም ድምጸት ያላቸውን ዐረፍተ ነገሮች እንዲለዩ ያድርጉ፡፡ ተጨማሪ ዐውዶችንም በራስዎ ይፍጠሩላቸውና የቋንቋ አጠቃቀሙን በእርስዎ መሪነት እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡

## ለ ማንበብ

### ትምህርት ሁለት፡- አጫጭር ልቦለዶችን ማንበብ

መምህር/ት፣

በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች በራሳቸው ፍጥነት አጫጭር ልቦለዶችን እንዲያነቡ ይጠበቃል፡፡ አጭር ልቦለድን በተመለከተ በተማሪው መጽሐፍ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ በማድረግ ስለ አጭር ልቦለድ ግንዛቤ ያስጨብጧቸው፡፡ በማስከተልም የተለያዩ አጫጭር ልቦለዶችን በንባብ ያስደምጧቸው፡፡ ከዚያም ሌሎች አጫጭር ልቦለዶችን የሚያገኙባቸውን መጽሐፍት በመጠቆም በራሳቸው ፍጥነት በቤታው እንዲያነቡ ያድርጓቸውና ታሪኩን ጽፈው በማምጣት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡

### ትምህርት ሦስት፡- የልቦለድ አላባውያንን መለየት

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ከልቦለድ ውስጥ ዋና ገጸ ባህርያትንና መቼትን እንዲለዩ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም የገጸ ባህርያትንና የመቼትን ምንነት አስመልክቶ ግንዛቤ ይፈጥርላቸው ዘንድ በመማሪያ መጽሐፍ ማስታወሻ ክፍል የቀረበውን ገለጻ

ተማሪዎችን ባሰተፈ መልኩ ያብራሩላቸው፡፡ በማስከተልም በመማሪያ መጽሐፍ ላይ“ የጉለሌው ሰካራም” በሚል ርዕስ የቀረበውን አጭር ልቦለድ አንብበው የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

## 10.4. መርጃ መሳሪያ

- ናሙና አጫጭር ልቦለዶች

## 10.5. ግምገማ

- የንግግር ድምጸቶችን አዳምጠው መለየታቸውን መገምገም፤
- አጫጭር ልቦለዶችን ማንበባቸውን ማረጋገጥ፤
- ከልቦለድ ውስጥ ገጸ ባህርያትን መለየታቸውን ማረጋገጥ፤
- ከልቦለድ ውስጥ መቼትን መለየታቸውን ማረጋገጥ፡፡

# መርሃ ትምህርት

# አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ
# 7ኛ ክፍል

# የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት

## ምዕራፍ አንድ፦ የሀገር ፍቅር (6 ክፍለ ጊዜያት)

አጠቃላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፦ ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፣ ስለ ሀገር ፍቅር ያዳመጡትን ይናገራሉ፤ ስዕልችን ተመልክተው የተረዱትን ይናገራሉ፤ አንብበው የጽሑፉን ይዘት ያስረዳሉ፤ ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጣሉ፤ ጀምር ሀሳቦችን አጠናቀው ይጽፋሉ።

| የማዳመጥና የመናገር ብቃት፣የሕይወት ክህሎት፣ እንዲሁም የቃላትና የሰዋስው አጠቃቀም ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት እንዲሁም የሥነ ጽሑፍ ችሎታ | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • ስለ ሀገር ፍቅር የቀረበውን ምንባብ አዳምጦ ጥያቄዎችን መመለስ<br>• ሰዕሎችን ተመልክቶ መናገር<br>• የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር ግጥምን እያነበቡ መዘመር<br>• የህዝቦችን ተከባብሮ የመኖር ባህል መዳበር ጥቅም መናገር<br>• ስለ ሀገር ፍቅር ስሜት መናገር<br>• ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት | • አንብበው የተረዱትን የጽሑፍ ይዘት ማስረዳት<br>• ጀምር ሀሳቦችን አሟልቶ መጻፍ | • በቅድመ፣ በማዳመጥ ጊዜ እና በድህረ ማዳመጥ ተግባራት በንቃት እንዲሳተፉ ማበረታታት<br>• የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙርን እንዲዘምሩና መልዕክቱን እንዲናገሩ ማድረግ<br>• በቅድመ፣ በማንበብ ጊዜ እና በድህረ ማንበብ ተግባራት በንቃት እንዲሳተፉ ማበረታታት<br>• በምንባቡ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍቺ እንዲፈልጉ መምራት<br>• በጀምር የቀሩ ሀሳቦች ከራሳቸው አሟልተው እንዲጽፉ ማድረግ |

**ግምገማ፡**

- ስለ ሀገር ፍቅር ባዳመጡት መሠረት ጥያቄዎችን በትክክል መመለሳቸውን ማረጋገጥ፣
- ስለ ሀገር ፍቅር መገለጫዎች አንብበው የተረዱትን የጽሑፍ ይዘት በንግግር ማስረዳት መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን መገምገም፣
- ጅምር ሀሳቦችን ከራሳቸው አፍልቀው ማሟላታቸውን መከታተል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት፡- ኮቪድ 19 (7 ክፍለ ጊዜያት)

አጠቃላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፣ ባዳመጡት መሠሠረት ክፍት ቦታዎችን ያሟላሉ፤ ስለወቅታዊ ጉዳይ አዳምጠው ክርክርና ምልልስ ያደርጋሉ፤ ስለ ኮቪድ-19 አንብበው የተረዱትን ይናገራሉ፤ ኮቪድ-19ኝን በተመለከተ የግል ተሞክሮዎቻቸውን ይናገራሉ፤ ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ይሰጣሉ፤ ምዕላዶችን ያጣምራሉ፤ይነጥላሉ፤ ነጠላና ድርብ ዐረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡

| የማዳመጥና የመናገር ብቃት፣የሕይወት ክህሎት፣ እንዲሁም የቃላትና የሰዋስው አጠቃቀም ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት እንዲሁም የሥነ ጽሁፍ ችሎታ | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • ስለ ኮቪድ 19 አንብበው የተረዱትን መናገር<br>• ስዕል ተመልክቶ የማዳመጥ ጥያቄዎችን መመለስ<br>• በንባብ የቀረበ ጽሑፍን አዳምጦ ምልልስና ክርክር ማቅረብ<br>• ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት<br>• ምዕላዶችን ማጣመርና መነጠል | • በንባብ የቀረበ ጽሑፍን አዳምጦ የተጓደሉ ቦታዎችን ማሟላት<br>• የቀረበውን ጽሑፍ አንብቦ ዋና ሀሳብን መጻፍ | • በንባብ የቀረበ ጽሑፍን አዳምጠው የተጓደሉ ሀሳቦችን በአግባቡ እንዲያሟሉ ማድረግ<br>• በንባብ የቀረበ ጽሑፍን አዳምጠው በምልልስና መክርክር በንቃት ማሳተፍ<br>• በግል አንባበው ስለተረዱት ሀሳብ እንዲገልጹ ማበረታታት፣<br>• ለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡ ማበረታታት<br>• በቃል ውስጥ ነጻና ጥገኛ ምዕላዶችን እንዲለዩ መምራት<br>• ነጠላና ድርብ ዐረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ማበረታታት፡፡ |

**ግምገማ**

- በንባብ የቀረበ ጽሑፍን አዳምጠው የተጓደሉ ሀሳቦችን በአግባቡ ማሟላታቸውን መከታተል፣
- በንባብ የቀረበ ጽሑፍን አዳምጠው በምልልስና መክርክር በንቃት መሳተፋቸውን መከታተል፣
- ስለ ኮቪድ 19 የቀረበውን ጽሑፍ በግል አንባበው ስለተረዱት ሀሳብ መግለጽ መቻላቸውን መገምገም፣
- ለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን መገምገም፣
- በቃል ውስጥ ነጻና ጥገኛ ምዕላዶችን ለይተው ማስቀመጣቸውን ማረጋገጥ፣
- ነጠላ ድርብ ዐረፍተ ነገሮችን መመስረታቸውን ማረጋገጥ።

## ምዕራፍ ሦስት፡- የአየር ንብረት (12 ክፍለ ጊዜያት)

አጠቃላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፣ አዳምጠው የተረዱትን ይናገራሉ፤ የድምፅ ጥብቀትን አዳምጠው ይለያሉ፤ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ንግግር ያደርጋሉ፤ በዐረፍተ ነገር ውስጥ ሥርዓተ ነጥቦችን ይጠቀማሉ፤ የተለያዩ የንባብ ስልቶችን ይለያሉ፤ ግጥም አንብበው ለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ ይሰጣሉ፤ የቃል ክፍሎችን ይለያሉ፡፡

| የማዳመጥና የመናገር ብቃት፣የሕይወት ክህሎት፣ እንዲሁም የቃላትና የሰዋስው አጠቃቀም ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት እንዲሁም የሥነ ጽሁፍ ችሎታ | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • አዳምጠው የተረዱትን መናገር<br>• የድምፅ ጥብቀትን አዳምጦ መለየት<br>• በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ንግግር ማቅረብ<br>• ሥርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ መገልገል<br>• የቃል ክፍሎችን መለየት | • የንባብ ስልቶችን መለየት<br>• ግጥምን አንብቦ ለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት | • የድምፅ ጥብቀትን አዳምጠው እንዲለዩ አቅጣጫ ማሳየት<br>• የንግግር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ንግግር እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት<br>• የንባብ ስልቶችን እንዲለዩ ማበረታታት<br>• ግጥምን አንብበው ለቃላት ተመሳሳና ተቀራኒ ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ<br>• ሥርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ እንዲጠቀሙ አቅጣጫ ማሳየት<br>• የቃል ክፍሎችን እንዲለዩ ማድረግ |

**ግምገማ**

- የድምፅ ጥብቀትን አዳምጠው መለየታቸውን ማረጋገጥ
- በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የንግግር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ንግግር ማቅረባቸውን ማረጋገጥ
- የንባብ ስልቶችን መለየታቸውን መከታተል
- ግጥምን አንብበው ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠታቸውን መከታተል
- ሥርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ መጠቀማቸውን ማረጋገጥ
- የቃል ክፍሎችን መለየታቸውን መገምገም

## ምዕራፍ አራት፡- ሥርዓተ ፆታ (9 ክፍለ ጊዜያት)

**አጠቃላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-** ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፣ ሥርዓተ ፆታን የተመለከተ ምንባብን አዳምጠው የተረዱትን ይገልጻሉ፤ በታቀደ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተቀናጀ ንግግር ያደርጋሉ፤ ቃላትን ለመረዳት ጽሑፍን ያነባሉ፤ አጣማሪዎችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ ይጠቀማሉ፤ የዐረፍተ ነገር ክፍሎችን ይለያሉ፤ በዐረፍተ ነገር ደረጃ ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በትክክል ይጠቀማሉ፡፡

| የማዳመጥና የመናገር ብቃት፣የሕይወት ክህሎት፣ እንዲሁም የቃላትና የሰዋስው አጠቃቀም ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት እንዲሁም የሥነ ጽሑፍ ችሎታ | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • ስለ ሥርዓተ ፆታ አዳምጠው የተረዱትን መናገር<br>• በታቀደ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተቀናጀ ንግግር ማቅረብ<br>• የዐረፍተ ነገር ክፍሎችን መለየት<br>• ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል መጠቀም | • ቃላትን ለመረዳት ማንበብ<br>• አጣማሪዎችን(አያያዦችን) በዐረፍተ ነገር ውስጥ መጠቀም<br>• የሰዋስው ስህተት ያለባቸውን ዐረፍተ ነገሮች አስተካክላችሁ መጻፍ | • ስለ ሥርዓተ ፆታ አዳምጠው የተረዱትን በጥያቄዎች መፈተሽ<br>• በታቀደ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተቀናጀ ንግግር እንዲያቀርቡ ማበረታታት፣<br>• ካነበቡት ጽሑፍ ውስጥ ለቀረቡ ቃላት ትክክለኛውን ፍቺ እንዲሰጡ ማበረታታት፤<br>• አጣማሪዎችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ እንዲጠቀሙ ማበረታታት፣<br>• የዐረፍተ ነገር ክፍሎችን በአግባቡ እንዲለዩ ማድረግ፣<br>• ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል እንዲጠቀሙ መምራት፡፡ |

## ግምገማ

- ስለ ሥርዓተ ፆታ አዳምጠው መረዳታቸውን በጥያቄዎች መገምገም፣
- በታቀደ ርዕሰ ጉዳይ የተቀናጀ ንግግር ማቅረባቸውን መከታተል፣
- ካነበቡት ጽሑፍ ውስጥ ለቀረቡ ቃላት ትክክለኛውን ፍቺ መስጠታቸውን ማረጋገጥ፣
- አጣማሪዎችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ መጠቀማቸውን ማረጋገጥ፣
- የዐረፍተ ነገር ክፍሎችን በአግባቡ መለየታቸውን መገምገም፣
- ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል መጠቀማቸውን መከታተል፡፡

## ምዕራፍ አምስት፡- ኑ ግብር እንክፈል (10 ክፍለ ጊዜያት)

**አጠቃላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-** ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፣ የተለያየ ድምጸት ያላቸውን ዐረፍተ ነገሮች አዳምጠው ይለያሉ፤ በድምጽ የተቀረጹ የግብር ማስታወቂያዎችን አዳምጠው ምላሽ ይሰጣሉ፤ በምልልሶች በንቃት ይሳተፋሉ፤ የምባቡን ይዘት ይተነትናሉ፤ አንቀጽ ይጽፋሉ፤ ጥሩ ተናጋሪዎች ቃላትን እንዴት በትክክል እንደሚጠሩ ይገመግማሉ፡፡

| የማዳመጥና የመናገር ብቃት፣ የሕይወት ክህሎት፣ እንዲሁም የቃላትና የሰዋስው አጠቃቀም ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት እንዲሁም የሥነ ጽሁፍ ችሎታ | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • የተለያየ ድምጸት ያላቸውን ዐረፍተ ነገሮች አዳምጦ መለየት<br>• በድምጽ የተቀረፁ የግብር ማስታወቂያዎችን አዳምጦ ምላሽ መስጠት<br>• በምልልሶች በንቃት መሳተፍ<br>• ቃላትን በትክክል መጥራት | • የምንባብን ይዘት መተንተን<br>• አንቀጽ መጻፍ | • ስለ ሥርዓተ ፆታ አዳምጠው የተረዱትን እንዲገልጹ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• በታቀደ ርዕሰ ጉዳይ የተቀናጀ ንግግር እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት<br>• ካነበቡት ጽሑፍ ውስጥ ለቀረቡ ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ በጥያቄዎች ማሳተፍ<br>• አጣማሪዎችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ እንዲጠቀሙ በምሳሌዎች መምራት<br>• የዐረፍተ ነገር ክፍሎችን ለይተው እንዲያስቀምጡ ማድረግ<br>• ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል እንዲጠቀሙ ማድረግ |

## ግምገማ

- ስለ ሥርዓተ ፆታ አዳምጠው መረዳታቸውን በጥያቄዎች መገምገም፣
- በታቀደ ርዕሰ ጉዳይ የተቀናጀ ንግግር ማቅረባቸውን መከታተል፣
- ካነበቡት ጽሑፍ ውስጥ ለቀረቡ ቃላት ትክክለኛውን ፍቺ መስጠታቸውን ማረጋገጥ፣
- አጣማሪዎችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ መጠቀማቸውን ማረጋገጥ፣
- የዐረፍተ ነገር ክፍሎችን በአግባቡ መለየታቸውን መገምገም፣
- ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በዐረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል መጠቀማቸውን መከታተል።

## ምዕራፍ ስድስት፡- ሳይንስና ቴክኖሎጂ (10 ክፍለ ጊዜያት)

አጠቃላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፣ ምልክቶችን አይተው ከሚደመጡ ቃላዊ ገለጻዎች ጋር ያዛምዳሉ፤ አዳምጠው የተረዱትን ይናገራሉ፤ በሚና ጨዋታ ይሳተፋሉ፤ በምንባብ የቀረቡ መመሪያዎችን አንብበው የተረዱትን ይገልጻሉ፤ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጽሁፎችን አንብበው ይዘቱን ይተነትናሉ ፤ የጽህፈት ደረጃዎችን ይዘረዝራሉ፤ የግጥም አነባበብ ስልትን ተከትለው ግጥም ያነባሉ።

| የማዳመጥና የመናገር ብቃት፣ የሕይወት ክህሎት፣ እንዲሁም የቃላትና የሰዋስው አጠቃቀም ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት እንዲሁም የሥነ ጽሑፍ ችሎታ | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • ምልክቶችን አይቶ ከሚደመጡ ቃላዊ ገለጻዎች ጋር ማዛመድ<br>• አዳምጠው የተረዱትን መናገር<br>• በሚና ጨዋታ መሳተፍ | • በምንባብ የቀረቡ መመሪያዎችን አንብቦ መግለጽ<br>• የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጽሑፎችን አንብቦ ይዘታቸውን መተንተን<br>• የጽህፈት ደረጃዎችን መዘርዘር<br>• ግጥም ማንበብ | • ምልክቶችን አይተው ከሚደመጡ ቃላዊ ገለጻዎች ጋር እንዲያዛምዱ ማድረግ<br>• በታቀደ የሚና ጨዋታ በንቃት እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት<br>• በንባብ የቀረቡ መመሪያዎችን እንዲተገብሩ ማድረግ<br>• የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጽሑፎች አንብበው ይዘታቸውን እንዲተነትኑ በጥያቄዎች ማነቃቃት<br>• የጽህፈት ደረጃዎችን እንዲተነትኑ ማድረግ |

## ግምገማ

- ምልክቶችን አይቶ ከሚደመጥ ቃላዊ ገለጻዎች ጋር ማዛመድ መቻላቸውን መከታተል
- በታቀደ የሚና ጨወታ በንቃት መሳተፋቸውን መከታተል
- በንባብ የቀረቡ መመሪያዎችን መተግበር መቻላቸውን ማጣራት
- የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጽሑፎች አንብበው ይዘታቸውን መተንተናቸውን በጥያቄ መፈተሽ
- የጽህፈት ደረጃዎችን መዘርዘራቸውን መከታተል

## ምዕራፍ ሰባት፡- ልዩ ፍላጎት (10 ክፍለ ጊዜያት)

**አጠቃላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-** ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፣ ባዳመጡት መሠረት ክፍት ቦታዎችን ያሟላሉ፤ በልዩ ፍላጎት ላይ ያተኮሩ ጉዳዮችን አዳምጠው ይወያያሉ፤ በሚና ጨወታ ውስጥ ይሳተፋሉ፤ በአካቶ ትምህርት ላይ የቀረበውን ጽሑፍ አንብበው አስተያየት ይሰጣሉ፤ በሕይወት ተሞክሮዎቻቸው ላይ ሰፋ ያለ አንቀጽ ይጽፋሉ፤ የማመልከቻ ደብዳቤ ይጽፋሉ።

| የማዳመጥና የመናገር ብቃት፣ የሕይወት ክህሎት፣ እንዲሁም የቃላትና የሰዋስው አጠቃቀም ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት እንዲሁም የሥነ ጽሑፍ ችሎታ | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • ባዳመጡት መሰረት ክፍት ቦታዎችን ማሟላት<br>• በሚና ጨወታ መሳተፍ<br>• በአካቶ ትምህርት ላይ የቀረበውን ጽሑፍ አንብቦ አስተያየት መስጠት | • አንቀጽ መጻፍ<br>• የማመልከቻ ደብዳቤ | • ባዳመጡት መሠረት ክፍት ቦታዎችን እንዲያሟሉ ማገዝ<br>• በሚና ጨወታ በንቃት እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት<br>• በአካቶ ትምህርት ላይ የቀረበውን ጽሑፍ አንብበው አስተያየት እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት<br>• ስለአካል ጉዳተኝነት አንቀጽ እንዲጽፉ ማበረታታት<br>• የማመልከቻ ደብዳቤ አጻጻፍ ሥርዓትን ተከትለው እንዲጽፉ ማድረግ |

## ግምገማ

- ባዳመጡት መሠረት ክፍት ቦታዎችን ማሟላታቸውን ማረጋገጥ
- በሚና ጫወታ በንቃት መሳተፋቸውን መከታተል
- በአካቶ ትምህርት ላይ የቀረበውን ጽሑፍ አንብበው አስተያየት መስጠታቸውን መገምገም
- ስለአካል ጉዳተኝነት የጻፉትን አንቀጽ መገምገም
- የማመልከቻ ደብዳቤ አጻጻፍ ሥርዓትን በመከተል መጻፋቸውን ማረጋገጥ

## ምዕራፍ ስምንት፡- ሱስና መዘዙ (10 ክፍለ ጊዜያት)

**አጠቃላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-** ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፣ ሱስና መዘዙ የሚለውን ጽሑፍ አዳምጠው የተረዱትን ይናገራሉ፤ የሱስ መከላከያ ዘዴን በሚመለከት የባለሙያ ምክር አዳምጠው ይናገራሉ፤ በተለያዩ ሀሳቦች ላይ ማጠቃለያ ሀሳብ ያፈልቃሉ፤ በሱሰኝነት የሚያውቁትን ሰው ታሪክ ይናገራሉ፤ በተማሪዎች ፊት ክርክር ያደርጋሉ፤ አንብበው በተረዱት መሠረት ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፤ የሕይወት ታሪክ ይጽፋሉ፤ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ይጽፋሉ፡፡

| የማዳመጥና የመናገር ብቃት፣ የሕይወት ክህሎት፣ እንዲሁም የቃላትና የሰዋስው አጠቃቀም ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት እንዲሁም የሥነ ጽሑፍ ችሎታ | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • አዳምጦ የጽሑፍን ፍሬ ነገር መናገር<br>• በማዳመጥ የተገኘ ሀሳብን ማጠቃለል<br>• ታሪክ መናገር<br>• የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ | • አንብቦ መረዳት<br>• የሕይወት ታሪክ መጻፍ<br>ምሳሌያዊ ንግግሮች | • አዳምጦ የጽሑፉን ፍሬ ነገር እንዲናገሩ ማድረግ<br>• በማዳመጥ የተገኘ ሀሳብ እንዲያጠቃልሉ ማበረታታት<br>• ታሪክ እንዲናገሩ ማድረግ<br>• ስለሱሰኝነት የቀረበውን ምንባብ አንብበው የተረዱትን በጥያቄ መፈተሽ<br>• የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ መመሪያን ተከትለው የሕይወት ታሪክ እንዲጽፉ ማድረግ |

## ግምገማ

- አዳምጦ የጽሑፉን ፍሬ ነገር መናገራቸውን መከታተል
- በማዳመጥ የተገኘ ሀሳብ ማጠቃለላቸውንና ታሪክ መናገራቸውን መከታተል
- ስለሱሰኝነት የቀረበውን ምንባብ አንብበው መረዳታቸውን በጥያቄ መፈተሽ
- የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ መመሪያን ተከትለው የሕይወት ታሪክ መጻፋቸውን መገምገም

## ምዕራፍ ዘጠኝ፡- ሀገር በቀል ዕውቀቶች (12 ክፍለ ጊዜያት)

**አጠቃላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-** ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፣ ያዳመጡትን ሀገር በቀል ዕውቀት መሠረት በማድረግ ልምድ ይለዋወጣሉ፤ ስለሀገር በቀል ዕውቀት አንብበው የተረዱትን ይናገራሉ፤ በተለያዩ ማህበራዊ ዐውዶች ውስጥ በሚታዩ የንግግርና የሰላምታ አቀራረብ ሁኔታዎች ላይ ልምድ ይለዋወጣሉ፤ ድርሰት ይጽፋሉ፤ በጠንካራ ሰራተኝነት ባህል ላይ ትኩረት ያደረገ ጽሑፍ ይጽፋሉ፤ የተረቶችን ዋና ሀሳብ ይናገራሉ፤ አፈ ታሪኮችን ይናገራሉ።

| የማዳመጥና የመናገር ብቃት፣ የህይወት ክህሎት፣ እንዲሁም የቃላትና የሰዋስው አጠቃቀም ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት እንዲሁም የሥነ ጽሁፍ ችሎታ | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • ባዳመጡት ሀገር በቀል ዕውቀት መሰረት ልምድ መለዋወጥ<br>• ስለሀገር በቀል ዕውቀት አንብበው የተረዱትን መናገር<br>• በተለያዩ ማህበራዊ ዐውዶች ውስጥ መናገር | • ድርሰት መጻፍ<br>• የተረቶችን ዋና ሀሳብ መናገር<br>• አፈ ታሪኮችን መናገር | • የንግግር ድምጸቶችን አዳምጠው እንዲለዩ ማድረግ<br>• አጫጭር ልቦለዶች እንዲያነቡ ማበረታታት<br>• ከልቦለድ ውስጥ ገጸ ባህሪያትን እንዲለዩ ማበረታታት<br>• ከልቦለድ ውስጥ መቼትን እንዲለዩ ማበረታታት |

## ግምገማ

- የንግግር ድምጸቶችን አዳምጠው መለየታቸውን መገምገም
- አጫጭር ልቦለዶችን ማንበባቸውን ማረጋገጥ
- ከልቦለድ ውስጥ ገጸ ባህሪያትን መለየታቸውን ማረጋገጥ
- ከልቦለድ ውስጥ መቼትን መለየታቸውን ማረጋገጥ

## ምዕራፍ አስር፡- አጭር ልቦለድ (8 ክፍለ ጊዜያት)

**አጠቃላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-** ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፣ የንግግር ድምጸቶችን አዳምጠው ይለማመዳሉ፤ በራሳቸው ፍጥነት አጫጭር ልቦለዶችን ያነባሉ፤ የልቦለድ አላባውያን (ገፀ ባህርይና መቼትን) ይለያሉ፡፡

| የማዳመጥና የመናገር ብቃት፣ የህይወት ክህሎት፣ እንዲሁም የቃላትና የሰዋስው አጠቃቀም ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት እንዲሁም የሥነ ጽሑፍ ችሎታ | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • የንግግር ድምጸቶችን አዳምጦ መለየት | • አጫጭር ልቦለዶችን ማንበብ<br>• የልቦለድ አላባውያንን መለየት | • የንግግር ድምጸቶችን አዳምጠው መልመጃዎች<br>• አጫጭር ልቦለዶችን እንዲያነቡ ልምምዶችን መስጠት<br>• ከልቦለድ ውስጥ ገጸ ባህርያትን እንዲለዩ ተግባራትን መስጠት<br>• ከልቦለድ ውስጥ መቼትን እንዲለዩ ተግባራትን መስጠት |

## ግምገማ

- የንግግር ድምጸቶችን አዳምጠው መለየታቸውን መገምገም
- አጫጭር ልቦለዶችን ማንበባቸውን ማረጋገጥ
- ከልቦለድ ውስጥ ገጸ ባህርያትን መለየታቸውን ማረጋገጥ
- ከልቦለድ ውስጥ መቼትን መለየታቸውን ማረጋገጥ